
# የብሔራዊ ክልል፣ ዞን እና ልዩ ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች በኢትዮጵያ ፤ ምክንያቶች፣ ተግዳሮቶች እና የመፍትሄ ሃሳቦች






አርታዒ
አበራ ወ/ኪዳን አሸብር

# የብሔራዊ ክልል፣ ዞን እና ልዩ ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች በኢትዮጵያ፤ ምክንያቶች፣ተግዳሮቶች እና የመፍትሄ ሃሳቦች


አርታዒ

አበራ ወ/ኪዳን አሸብር



2015

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

© 2015 ዓ.ም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
አዲስ አበባ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው
ISBN: 978-99944-50-79-4

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል፡ fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

ይህ ህትመት በፍሬደሪክ ኤበርት ስቲፍቱንግ ፋውንዴሽን (Friedrich Ebert Stiftung-FES) ድጋፍ የተደረገውን ውይይት መሰረት አድርጎ በዲጂታል መንገድ የታተመ ነው። በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱት ፅሁፎችና እና የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርድን፣የድርጅቱን አጋሮችና ለውይይቱ የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን ፍሬደሪክ ኤበርት ስቲፍቱንግ ፋውንዴሽን አቋምና አመለካከት፤ ላያንጸባርቅ ይችላል።

# ማውጫ


*መቅድም* ……………………………………………………………………2

I. የኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት አወቃቀር እና የክልልነት ጥያቄዎች

*አስናቀ ከፍአለ* ………………………………………………………………9

II. በኢትዮጵያ ፌደሬሽን የክልል፣ዞን እና ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች እና የመፍትሄ ሃሳቦች

*ኃይለየሱስ ታዬ*……………………………………………………………..19

III. አለመተማመን እና የመዋቅር ጥያቄ በኢትዮጵያ

*ገብሬ ይንቲሶ ደኮ*…………………………………………………………..29

IV. ለዲሞክራሲያዊ ፌዴራል ሥርዓት መገንባት አንዳንድ አስተያየት

*አንዷርጋቸው አሰግድ*………………………………………………………41

## መቅድም

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ.ኤስ.ኤስ.) በተለያዩ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ምርምር በማካሄድ እና ህዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የሚመለከታቸውን የመንግስት ባለ ስልጣናትን ጨምሮ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት እንዲሳተፉ በመጋበዝ የፖሊሲ አወጣጥ ሂደቱ በመረጃ የተደገፈ እና አሳታፊ እንዲሆን የራሱን አስተዋፅኦ ሲያበረክት የቆየ መንግስታዊ ያልሆነ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ሃገር-በቀል ሃሳብ አመንጭ ተቋም ነው።

ድርጅቱ በ25 ዓመታት ቆይታው በበርካታ የልማት እና ልማት-ነክ በሆኑ ጉዳዮች (ለምሳሌ፤ ድህነት ቅነሳ፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ወጣቶች እና ልማት፣ ሴቶቸ ጉዳይ የዲሞክራሲ እና መስተዳድር፣ የወጭ ጉዳይ ፖሊሲ) እና ሌሎችም አበይት ሀገራዊ ጉዳዮችቸ ዙርያ የፖሊሲ ጥናት አካሂዷል፣ የህዝባዊ የውይይት መድረኮችን አዘጋጅቷል። የጥናትና ውይይት ውጤቶችንም በተለያዩ ህትመቶች (ማለትም በመፅሃፍ፣ በሞኖግራፍ እና በፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች) መልክ ለፖሊሲ አውጪዎች ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል። ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን (በኤፍ.ኤም. ራድዮ ጣቢያዎች) እና የድርጅቱ ኦፊሴላዊ ድረ-ገፅን ጨምሮ በዩ-ትዩብ እና በተለያዩ የማኅበራዊ ትስስር ገፆች አማካኝነት ለባለ ድርሻ አካላት እና ለህዝብ አቅርቧል።

*"ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ጉዞ በኢትዮጰያ"* እና *"መሬት እና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ"* የተሰኙት ድርጅቱ በቅርብ ዓመታት ምርምሮች እና ውይይት ያካሄደባቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ የህዝባዊ ውይይት መድረኮች ለአንድ ዓመት እና ከዚያም በላይ የሚዘልቁ በየወሩ በመደበኛነት የሚካሔዱ ነበሩ።

ኤፍ.ኤስ.ኤስ.፤ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በተለይ ባለፉት አራት አመታት በአገሪቱ የተጀመረውን ለውጥ ተከትለው በተስተዋሉ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ያልሆኑ የውይይት መድረኮችን አዘጋጅቷል፤ ጉዳዮቹ የሚመለከታቸውን አካላትም ጋብዞ አሳትፏል። ለምሳሌ፤ በቅርቡ የውጭ ባንኮች ሃገር ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ የሚፈቅድ የፖሊሲ ውሳኔ በሚኒስትሮች ም/ቤት መነሳቱን እና የሀገሪቱ የንግድ ህግም በመሻሻል ሂደት ውስጥ መግባቱን ተከትሎ፣ በአንድ በኩል የውጭ ባንኮቹ መግባት በአገር ውስጥ ባንኮች ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅእኖ ግምት ውስጥ በማስገባት እና በሌላም በኩል በንግድ ሕጉ ዙርያ በመንግሥት እየተካሄዱ ያሉ የማሻሻል ስራዎች ዓላማ እና ሂደት በቂ ግንዛቤ እንዲኖር በማሰብ በመረጃ የተደገፈ

የውይይት መርሃ-ግብር አካሂዶ ነበር፡፡ በዚህም መድረክ የዘርፉ ምሁራን የውይይት ወረቀት አቅርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። የውይይቱ መነሻ ወረቀቶች አጽርሀቶችም በድርጅቱ ድረ-ገጽ ላይ ተጭነው ይገኛሉ፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ ባለፉት አራት ዓመታት አገራችን ኢትዮጵያ ከገባችበት የዲሞክራሲ የለውጥ ጉዞ ጋር ተያይዞ በርካታ ክስተቶች የተስተዋሉ ሲሆን ከነዚህም ክስተቶች አንዱ በሃገሪቱ ሕገ-መንግሥት ላይ ተመስርተው የሚቀርቡ የአደረጃጀት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም የሲዳማ ብሔረሰብ የክልልነት ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱን ተከትሎ የብሔራዊ ክልልነት፣ ዞንነት እና ልዩ ወረዳ እንሁን ጥያቄዎች ተበራክተው ቀጥለዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለወደፊትም ሊቀጥል እንደሚችል በዘርፉ ያሉ ምሁራን እና ተመራማሪዎች ይናገራሉ፡፡

ኤፍ.ኤስ.ኤስ፤ ይህ ራሰን በራሰ የማስተዳደር ጥያቄ ማብቂያው የት ነው? መንግሥስት እነዚህን ጥያቄዎቸ የሚያስተናግድበት አግባብ ምን መሆን አለበት? ሃገሪቱ በጀመረችው የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደቱስ ላይ ምን አይነት ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል? በሚሉ እና በሌሎችም ምላሽ የሚያሻቸው ተዛማጅ ጥያቄዎች ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ የማካሄድ አስፈላጊነትን ስላመነበት ከፍሬደሪክ ኤበርት ስቲፍቱንግ ፋውንዴሽን (Friedrich Ebert Stiftung-FES) ጋር በመተባበር ሐሙስ መስከረም 19 ቀን 2015 ዓ.ም. የግማሽ ቀን የውይይየት መድረክ በኢንተር-ላግዠሪ ሆቴል አዘጋጅቶ ነበር፡፡

በዋናነት ብሔራዊ ክልል፣ ዞን እና ልዩ ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ያተኮረው የውይይት መድረክ ዋና ዓላማ የአደረጃጀት እና የመዋቅር ጥያቄዎች እንዲነሱ የሚገፋፉ መሰረታዊ ምክንያቶችን መዳሰስ እና ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት የሚረዱ ምክረ-ሃሳቦችን ለመንግሥት በማቅረብ በሃገራችን የተጀመረው የለውጥ ጉዞ ያለ እንቅፋት ማስቀጠል እንዲቻል ማገዝ ነው፡፡

ውይይቱ የተካሄደው *"እየተበራከተ የመጣው ብሔራዊ ክልል፣ ዞን እና ልዩ ወረዳ የመሆን ጥያቄ፤ እናም ይህ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ"* በሚል ርእስ ሲሆን በዚህ ርዕስ ዙርያ የሚያጠነጥኑ አራት ጥናታዊ ጽሁፎች በሶስት ምሁራንና ተመራማሪዎች እንዲሁም አንድ አንጋፋ የፖለቲካ ሰው ቀርበዋል፡፡ በቀረቡት ጽሁፎችም ላይ ሰፊ ውይይት በተሳታፊዎች ተካሂዷል፡፡

ኤፍ.ኤስ.ኤስ. በውይይቱ ተገኝተው ለተሳተፉ እና ጥናታዊ ፅሁፎቻቸውን ላቀረቡ ምሁራን እንዲሁም የውይይት መድረኩን ለማዘጋጀት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገው

በኢትዮጵያ የፍሬደሪክ ኤበርት ስቲፍቱንግ ፋውንዴሽን ከፍ ያለ ምስጋና እያቀረበ፤ ሁሌም እንደሚያደርገው የቀረቡት ወረቀቶች ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለባለ ድርሻ አካላት እና ለህዝብ ተደራሽ ይሆኑ ዘንድ አስፈላጊው አርትኦት ተደርጎባቸው ቀጥለው ሰፍረዋል።

የቀረቡት ወረቀቶች ረዕስ እና አቅራቢዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

1. የኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት አወቃቀርና የክልልነት ጥያቄዎች (ዶ/ር አስናቀ ከፍአለ)፣
2. በኢትዮጵያ ፌደሬሽን የክልል፤ዞን እና ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች እና የመፍትሄ ሃሳቦች (ዶ/ር ኃይለየሱስ ታዬ)፣
3. አለመተማመን እና የመዋቅር ጥያቄ በኢትዮጵያ (ፕሮፌሰር ገብሬ ይንቲሶ ደኮ)፣
4. ለዲሞክራሲያዊ ፌዴራል ሥርዓት መገንባት አንዳንድ አስተያየት (አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ)።

አርታኢ፡ አበራ ወ/ኪዳን አሸብር

ጥቅምት 2015 ዓ.ም.

# I. የኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት አወቃቀርና የክልልነት ጥያቄዎች

አስናቀ ከፍአለ

## 1. መግቢያ

የዚህ ጽሁፍ አላማ የራስን በራስ የማስተዳደር (በተለይም የክልል) ጥያቄዎች እንዲነሱ የሚገፋፉ ምክንያቶችን መዳሰስ እና ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት የሚረዱ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ነው:: ይህ ፅሁፍ የመጀመርያ የሆነው የመግቢያውን ክፍል ጨመሮ አምስት ክፍሎች ሲኖሩት፤ ሁለተኛው ክፍል የአዲስ ክልል ምስረታን በተመለከተ ኢትዮጵያና ሌሎች የፌደራል ስርዓት የሚከተሉ አገሮች የሚከተሏቸው አሰራሮችን እና መርሆዎችን በአጭሩ ይዳስሳል:: ሶስተኛው ክፍል የክልልና ሌሎች የአስተዳደር መዋቅር ጥያቄዎች እንዲነሱ የሚያደርጉ ዋና ዋና ምክንያቶችን ይተነትናል:: በመጨረሻም በአራተኛ እና በአምስተኛ ክፍሎች-እንደ ቅደም ተከተሉ- የማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ይቀርባሉ::

## 2. የአዲስ ክልል ምስረታ በኢትዮጵያ እና በሌሎች የፌደራል ስርዓትን የሚከተሉ አገሮች

የኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት አወቃቀር በዋናነት መሰረት አድርጎ የሚነሳው ብሔር-ብሔረሰቦችን ስለሆነ ብሔር-ብሔረሰቦች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች እንደሆኑ ይደነግጋል::

የሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 39 ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር- ብሔረሰብና ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ እንደሆነ ያትታል:: በአንቀፅ 39 ላይ እንደተዘረዘረው የኢትዮጵያ ብሔር- ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት በራሳቸው መልከዓ-ምድር ውስጥ ራስን በራስ ማስተዳደር እና በክልልና በፌደራል (ማዕከላዊ) አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና እንዲኖራቸው ግዴታ ያስቀምጣል::

የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 46/2 ክልሎች ሲዋቀሩ የህዝብ አሰፋፈርን፣ ቋንቋን፣ ማንነትን እና ፈቃድን መሠረት ያደረገ እንደሚሆን ያስቀምጣል። በዚህ መስፈርት መሠረትም 9 ክልሎች መቋቋማቸውን በአንቀፅ 47(1) ላይ ይዘረዝራል። ነገር ግን በኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ የሚሆኑ ብሄረሰቦች እንደሚገኙ ይታወቃል። ይህ ማለት በሕገ-መንግስቱ ለሁሉም ብሔረሰቦች የተሰጠው ክልል የማቋቋም መብት በተግባር ላይ ቢውል በኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ 80 ክልሎች ይኖሩ ነበር። መሬት ላይ ያለው ሀቅ ግን ከዚህ የተለየ ነው። ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ውስጥ በክልል ደረጃ የተዋቀሩት 6 የሚሆኑት ብቻ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ብሔረሰቦች የተዋቀሩት ከክልል በታች ባሉ ራስን በራስ የማስተዳደር አደረጃጀት ነው።

በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 47 (3) በተጠቀሰው መሠረት ብሔር/ብሔረሰቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብታቸው ያለገደብ የተፈቀደ እንደሆነ ያስቀምጣል። በዚህ አንቀፅ መሠረት እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱን ክልል ለማቋቋም የሚጠበቅበት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሂደቶች ማከናወን ብቻ ይሆናል፦

1) የክልል መመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በህዝቡ ምክር ቤት በሁለት/ሦስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በፅሁፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣
2) ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ህዝበ - ውሳኔ ሲያደራጅ፤
3) ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በህዝቡ ህዝበ-ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፣
4) የክልሉ ምክር ቤት ስልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ሲያስረክብ፤
5) በህዝበ - ውሳኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት አንቀጾች የአካሄድ ሥርዓቶችን እንጂ፤ ሕገ-መንግሥቱ በክልል ደረጃ ለመደራጀት መሟላት የሚገባቸው ምንም ዓይነት ግዴታዎችን አያስቀምጥም። በዚህም መሠረት ጥያቄውን የሚያቀርበው ቡድን/ብሔረሰብ ብቻ ወሳኝ ይሆናል ማለት ነው። ሌሎች አካላት (ለምሳሌ ጥያቄው የሚቀርብበት ክልል ወይም ክልሉ ጥያቄውን መፍታት ካልቻለ የፌደሬሽን ምክር ቤት) ጉዳዩን በሕጉ መሠረት ከማስፈጸም የዘለለ ወይም በስምምነት ለመፍታት ከመሞከር ያለፈ ሚና አይኖራቸውም። ይህ አካሄድ ቀላል ከመሆኑ አኳያ የፌደራል ሥርዓቱ የተረጋጋ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ከሌሎች የፌደራል ሥርዓትን ከሚከተሉ ሀገሮች አሰራር አንፃር ሲታይ እጅጉን በጣም የተለየ እንዲሆን አድርጎታል።

አስናቀ ከፍአለ

አዲስ ክልል ምስረታን በተመለከተ ፌደራል መንግስታት ልዩ ልዩ መርሆዎች ይከተላሉ። አንዳንዶቹ የፌደራል ሀገሮች አዳዲስ ክልሎች ከነባር ክልሎች እንዳይመሰረቱ ከነአካቴው ሲከለክሉ ሌሎቹ ደግሞ አዳዲስ ክልሎችን መመስረት ያልተከለከለ ቢሆንም ሌሎች ክልሎች (በተለይ ጥያቄው የሚቀርብበት ክልል ወይም ክልሎች) እና የፌደራል መንግስቱ በሂደቱ የመሳተፍና የመወሰን ስልጣን እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።

ለምሳሌ አሜሪካንን ብንወስድ ፌደሬሽኑ የተቋቋመበት መንገድ ቀድሞ የታወቀ የየራሳቸው የአስተዳደር ወሰንና ሉዓላዊነት የነበራቸው ክልሎች የመሰረቱት በመሆኑ አዳዲስ ክልሎች ወደ ፌደሬሽኑ እንዲገቡ ይፈቅዳል እንጂ ከግዛቱ እንዲወጡ ወይም ከነባር ክልሎች አዳዲስ ክልሎች እንዲቋቋሙ  አይፈቅድም። የአሜሪካ ሕገ-መንግስት ክፍል 3  አዳዲስ ግዛቶች በምክር ቤቱ (ኮንግረሱ) ፈቃድ ወደ ፌደሬሽኑ ሊቀላቀሉ እንደሚችሉ ይደነግጋል።

የአውስትራሊያን ሕገ-መንግስት ብንመለከት ከአሜሪካው ሕገ-መንግስት ለየት ባለ መልኩ አዳዲስ ክልሎች ሊፈጠሩ (ሊቋቋሙ) እንደሚችሉ ይደነግጋል። ነገር ግን በሂደቱ ላይ የፌደራል መንግስቱ ፓርላማ የመወሰን ሚና እንዳለው ይደነግጋል።

በደቡብ አፍሪካ ሕገ-መንግስት መሠረት ደግሞ አዲስ ክልል ለማቋቋም የሕገ-መንግስት ማሻሻያ ማድረግን እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል። በዚህም መሠረት የክልሎችን ድንበር፣ ሥልጣን ወይም ተቋሞቻቸውን ለመለወጥ ከተፈለገ በአንቀጽ 74(3)(ii) ላይ የተቀመጠውና በማዕከላዊ ምክር ቤቱ 2/3ተኛ ድምፅና በ6 ክልል ምክር ቤቶች መደገፍ ያለበትን የሕገ-መንግስት ድንጋጌ ማሻሻያ ማለፍ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም ይህ የሕገ-መንግስት ማሻሻያ ጥያቄው በቀረበበት ክልል ምክር ቤት መፅደቅ አለበት። ብዙ ያልተረጋጋና በተለያዩ ጊዜያት ተጨማሪ ክልሎችን እያቋቋመ የመጣውን የናይጄሪያን ፌደሬሽን ብንመለከት ሃገሪቱ በ1960 ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነጻ ስትወጣ 3 ብቻ የነበሩት የፌደሬሽኑ አባል ክልሎች በተለያየ ወቅት ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቶ በአሁኑ ሰዓት ወደ 36 አድገዋል። በናይጄሪያ ብዙዎቹ አዳዲስ ክልሎች የተቋቋሙት በወታደራዊ አገዛዝ ዘመናት በመሆናቸው የሕገ-መንግስታዊ ሂደትን የጠበቁ ነበር ለማለት ያስቸግራል። ሆኖም በሲቪል አስተዳደር ወቅት የክልልነት ጥያቄ አልነበረም ማለት አይደለም። ጥያቄዎች በስፋት ይስተዋሉ ነበር። ነገር ግን ጉዳዩ የፖለቲካ ትኩሳትና የሕገ-መንግስት ማነቆነት ስለነበረበት እንደ ወታደራዊ አስተዳደሩ ግዜ በቀላሉ ሊፈፅሙት አልተቻላቸውም።

የ1999ኙን የናይጀሪያ ሕገ-መንግስት ክፍል II አንቀፅ 8(1) ስንመለከት አዳዲስ ክልሎች ሊቋቋሙ እንደሚችሉ በማስቀመጥ የሚቋቋሙበትን አካሄድ በግልፅ

ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሠረት የብሔራዊ ጉባዔው/ምክር ቤቱ የአዳዲስ ክልሎች መቋቋም ጥያቄን ሊያጸድቅ የሚችለው፡- 1) ጥያቄው የሚቀርብበት የክልል ምክር ቤት በ2/3ተኛ ድምፅ ሲደግፍ፣ 2) ጥያቄው በቀረበበት አካባቢ ነዋሪ በ2/3ተኛ የህዝበ ውሳኔ ድምፅ ሲደግፍ፣ 3) የህዝበ ውሳኔው ውጤት በአብዛኞቹ ክልሎች ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምፅ (50+1) ሲደገፍና 4) ክልል የመመስረት ጥያቄው በሀገሪቷ ብሄራዊ ጉባዔ 2/3ተኛ ድምፅ ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህ ማለት በናይጄሪያ አዲስ ክልል ማቋቋም የተከለከለ ባይሆንም እንደ ኢትዮጵያ በጠያቂው ወገን ብቻ የሚፈፀም አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር የጠያቂው አካል ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክልሎችና የፌደራል መንግሥቱ በሂደቱና በውጤቱ ላይ የወሳኝነት ሚና ይኖራቸዋል፡፡

ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ለውጦችን እያደረገ የመጣውን የህንድ ፌደሬሽን ስንመለከት አዳዲስ ክልሎች ማቋቋምም ይሁን ወደ ፌደሬሽኑ መቀላቀል በሕገ-መንግስቱ የተፈቀደ መብት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሥልጣን የተሰጠው ለፌደራሉ ፓርላማ ብቻ በመሆኑ ይህ ከሁሉም ፌደሬሽኖች ለየት ያደርገዋል፡፡ በ1949ኙ የህንድ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 3 መሠረት ፓርላማው ከማንኛውም ክልል በመነጠል አዲስ ክልል ሊያቋቁም አሊያም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክልሎችን በማዋሃድ አዲስ ክልል መፍጠር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት በ14 ክልሎችና በ6 የአንድነት ግዛቶች የጀመረው የህንድ ፌደሬሽን በአሁኑ ሰዓት 29 ክልሎችና 7 የአንድነት ግዛቶች አሉት፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የፌደራል ሀገሮች አዳዲስ ክልሎችን የማቋቋም መብቶቸን እና ጥያቄዎችን የማስተናገድ ተሞክሮዎች አንፃር የኢትዮጵያን ስንገመግመው ይህ መብት የተሰጠው ለጠያቂው ቡድን/ብሔረሰብ ብቻ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ይህም ማለት ጥያቄው የተነሳበት ክልልም ይሁን የፌደራል መንግሥቱ ጥያቄውን ተቀብለው ሂደቱን ከማስፈጸም የዘለለ ሚና የላቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት አዲስ በሚፈጠረው ክልል ውስጥ የሚኖሩ አናሳ ቁጥር ያላቸው ቡድኖችን/ብሔረሰቦችን መብት ለማስጠበቅ የሚገደድበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ሌላው ደግሞ ጠያቂው አካል ምንም ዓይነት ምክንያት ማቅረብ የማይጠበቅበት መሆኑና የአካሄድ ሥርዓቱም እጅግ ቀላል በመሆኑ አብዛኛዎቹ ብሔረሰቦች የክልልነት ጥያቄ ማቅረባቸውን የማይቀር ያደርገዋል፡፡

ለምሳሌ ያህል የሲዳማ ብሔረሰብ ዞን ባቀረበው ጥያቄ መሠረት እና የክልሉና የፌደራሉ የፌደሬሽን ምክር ቤቶች ሂደቱን በማሳለጥ ዞኑ የክልልነት ደረጃ አግኝቷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ሌሎች ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የክልል እንሁን ጥያቄያቸውን በምክር ቤቶቻቸው በማፀደቅ ለደቡብ ክልልና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አቅርበዋል (ወላይታን፣ ጉራጌን፣ ስልጤን፣ ሐዲያንና ሌሎችንም እንደማሳያ መጥቀስ

ይቻላል):: የክልሉ መንግሥት ወይም የፌደራሉ መንግሥት በሂደቱ ውስጥ የውሳኔ ሰጭነት ሚና በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ስለሌላቸው ጥያቄውን የሚገቱበት ሕጋዊ መሠረት አይኖራቸውም:: የፌደራሉ መንግስትና ገዢው ፓርቲ ከሲዳማና ከደቡብ ምዕራብ ክልሎች ምስረታ በኋላ ቀሪውን የደቡብ ክልል በሁለት (ክለስተር) ክልሎች ለማደራጀት በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው:: ይህ ሂደትም በበርካታ ውዝግቦች የታጀበ መሆኑ ይታወቃል:: በዚህም ምክንያት በእቅድ ላይ ያለው አደረጃጀት ዘላቂ መፍትሄ ያመጣል ብሎ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው::

## 3. ራስን በራስ የማስተዳደርና የክልል ምስረታ ጥያቄዎች ዋና ዋና መነሻ ምክንያቶች፡

ራስን በራስ የማስተዳደር (የክልል ምስረታ) ጥያቄዎች መነሻ ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም የተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታመናል:: ዋና ዋና ምክንያቶቹ ግን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፣ የፖለቲካ ውክልና/ተሳትፎ፣ የቋንቋ/ማንነት ጥያቄዎችና የመንግሥት አገልግሎት ተደራሽነት ማነስ ናቸው:: እነዚህ ምክንያቶች በአንድ ላይ ወይም በተናጠል የራስን በራስ የማስተዳደር (የክልል) ጥያቄዎች ምክንያቶች ሆነዋል::

### 3.1 ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች፤ በጀት፣ የተፈጥሮና ሌሎች ሃብቶች

የክልል ወይም ከፍ ያለ የአስተዳደር እርከን የሚጠይቁ የፖለቲካ ተዋናዮች ከፍ ያለ ራስን በራስ የማስተዳደር መዋቅር ቢሰጣቸው ወይም ክልል ቢመሰርቱ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው ይገነዘባሉ:: የክልል፣ ዞን፣ ልዩ ወረዳና የወረዳ መዋቅር ከመንግሥት የተሻለ በጀት እንዲያገኙ እንደሚያደርግና የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድል ሊፈጥር እንደሚችል ይገልጻሉ ፤ ደጋፊዎቻቸውንም በዚህ ዙርያ ያንቀሳቅሳሉ::

ሌላው ከኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረው የክልል ጥያቄ በራስ ሃብት፤ ማለትም መሬት፣ ማዕድን፣ ደን፣ የከተማ መሬትና የታክስ ገቢ የበለጠ ተጠቃሚ የመሆን እድል ይኖረናል የሚል ነው:: በተጨማሪም መንግሥት ከሚዘረጋቸው የልማት ሥራዎች የሥራ እድል ፈጠራን ጨምሮ በፍትሃዊነት ተጠቃሚ አለመሆን እንደ ምክንያት ይጠቀሳል::

## 3.2. የብሔረሰብ የፖለቲካ ልሂቃን ፍላጎቶችና የማዕከላዊ መንግስት አቋም

ከ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥ በኋላ የተደረጉ የመዋቅርና የሕግ ለውጦች- በተለይም የብሔረሰብ አደረጃጀት- በፖለቲካው በማየሉ ምክንያት በሁሉም ብሔረሰቦች የፖለቲካ ልሂቃን ተፈጥረዋል:: ለልሂቃኑ መፈጠርና መስፋፋት የኢሕአዴግ (አሁን ደግሞ የብልጽግና) አደረጃጀት፣ የብሔረሰቦች ውክልና በመንግስት ተቋማትና የትምህርት እድሎች መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: የፖለቲካ ልሂቃኑ የክልል መዋቅር የተሻለ ሥልጣንና ጥቅም ያመጣልናል በሚል እሳቤ የክልል ጥያቄውን የብሔረሰብ መብት ማስከበር በሚል ሽፋን ያንቀሳቅሱታል:: አብዛኛውን ጊዜ በገዢው ፓርቲ ውስጥ ያሉና በተቃዋሚ ጎራ የሚመደቡ የብሔረሰብ ፖለቲካ ልሂቃን በክልል ጥያቄ ዙሪያ ሲተባበሩ ይታያሉ::

ኢሕአዴግ ምንም እንኳን በሕገ-መንግስት የማንኛውንም ብሔረሰብ ክልል የመመስረት መብት ቢያረጋግጥም በተግባር ግን የክልል ምስረታ ጥያቄዎችን በፖለቲካ አሰራር (በኢሕአዴግ የፓርቲ አሰራር) ሲከላከል ቆይቷል:: ለምሳሌ ከሲዳማ የተነሳውን ጠንካራ የክልል ጥያቄ በሁለት መንገድ አፍኖት ነበረ:: በአንድ በኩል ለሲዳማ ፖለቲከኞች ከፍ ያለ ቦታ በደቡብ ክልል እንዲሰጣቸው ሲያደርግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥያቄው አራማጆች ላይ የጭቆና እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል::

በኢህአዴግ ዘመን የማዕከላዊው መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ጠንካራ የመቆጣጠር አቋም ላይ በነበሩበት ወቅት ተዳፍነው የነበሩት ጥያቄዎች በ2010 ዓ/ም ከተደረገው የመንግሥት ለውጥ በኋላ በሰፊው እየተነሱ ይገኛሉ:: በደቡብ ክልል ከሲዳማ ክልል መመስረት በኋላ አብዛኛዎቹ ዞኖች የክልል ጥያቄ አቅርበዋል::

## 3.3. የመልካም አስተዳደር እና የአገልግሎት ተደራሽነት ችግሮች

በተለያዩ ክልሎች የሚነሳው አንደኛው ራስን በራስ የማስተዳደር (የክልል፣ ዞንና ወረዳ) ጥያቄ ምክንያቱ ነዋሪዎች ለመንግስት አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆናቸው ነው:: አንዳንድ ክልሎች በጣም ሰፊ በመሆናቸውና የመንገድና የኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ተደራሽነት በጣም ውስን በመሆኑ የወረዳና የዞን ጥያቄዎች ይነሳሉ:: አንዳንድ አካባቢዎች ለዘመናት የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የመንገድ፣ የትምህርት ቤት፣ ባንክን ጨምሮ የፋይናንስ ተቋማት፣ የጤና አገልግሎት፣ እና የግብርና ግብአት አገልግሎቶች በተገቢው መንገድ ስለማይደርሷቸው ይህን ችግር ለመቅረፍ ሲባል የተሻለ የአስተዳደር እርከን ይጠይቃሉ:: የወረዳ ይመስረትልን ጥያቄ የብሔረሰብ ብዝሃነት ባላቸው ክልሎች ብቻ ሳይሆን የአንድ ብሔር የበላይነት ባላቸው ክልሎች ለምሳሌ ያህል በአማራ፣ ኦሮሚያና ሱማሌ ክልሎች ውስጥ በሰፊው ይንጸባረቃል:: በአንዳንድ አካባቢዎች ዜጎች አቤቱታቸውን ለወረዳ አስተዳደር ለማቅረብ ለምን ከ100

ኪሎ ሜትር በላይ እንጓዛለን በማለት ያነሳሉ። ሌሎቹ ደግሞ በፊት በነበረው (በደርግ ወይም ደግሞ በኢሕአዴግ) ወረዳ የነበሩ ቦታዎች ከቀድሞ ደረጃቸው ዝቅ ብለው ቀበሌ በመሆናቸው ቅሬታ አላቸው። የወረዳ መዋቅርም ይጠይቃሉ።

## 3.4. ማንነት፣ ውክልናና ተሳትፎ

የማንነት.፣ የውክልና የተሳትፎ ጥያቄ በተለይ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ሌላው ምክንያት ሆኗል። እንደዚህ አይነት ጥያቄ የሚያነሱ ማህበረሰቦች በቋንቋቸው መማር፣ መስራት እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን አለማግኘታቸውን እንደ አንድ ዋና ምክንያት ያቀርባሉ። እነዚህን ጥያቄዎች በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

**አንደኛ**፤ ሕብረ-ብሔራዊ መሆናቸውን በሕገ-መንግስታቸው በተቀበሉ ክልሎች (ደቡብ፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ) አንዳንድ ብሔረሰቦች የማንነት፣ የውክልና የተሳትፎ ጥያቄ  ያነሳሉ፤ በእነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ደም አፋሳሽ ግጭቶች ተክስተዋል። የፌደራሉ ሕገ-መንግስት የተለየ ማንነት ላላቸውና ነባር ለሚባሉ ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ስለሚፈቅድ እነዚህ ብሔረሰቦች አቤቱታቸውን ለወረዳ፣ ዞንና ክልል ምክርቤት በማቅረብ መልስ እየጠበቁ ይገኛሉ።

**ሁለተኛ**፤ በክልሎች አዋሳኝ ቦታዎች የሚነሱ የማንነትና የውክልና ጥያቄዎች ክልሎች በተመሰረቱበትና ድንበራቸው (ወሰናቸው) በሚሰመርበት ወቅት (እስከ አሁን በሕግ የታወቀ የክልል ድንበር/ወሰን ባይኖርም) በበርካታ ቦታዎች ማንነታቸው ወደ አንዱ ክልል ሆኖ ወደ ሌላው ክልል የተካለሉ ወይም ደግሞ የብሔረሰብና የቋንቋ ማንነታቸው ወደ አንድ ክልል ማምጣት አስቸጋሪ የሆኑ ቦታዎች ያለ በቂ  የህዝብ ተሳትፎ በፖለቲካ አሰራር ወደ አንዱ ክልል መካለል፤ የማንነት፣ ራስን በራስ የማስተዳደርና የወሰን (ድንበር) ጥያቄዎች አስከትለዋል። በኦሮሚያ- ሶማሌ፣ አማራ-ትግራይ፣ አፋር- ሶማሌ ክልሎች መሃከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ማየት ይቻላል።

**ሦስተኛ**፤ለብሔር ማነነትና በተለይም በግልፅ ባይነገርም ባለቤት (ነባር) እና መጤ(ሰፋሪ) የሚለው አስተሳሰብ ስር በመስደዱ ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ (ከክልላቸው ውጭ) ነው የሚኖሩት በሚለው እሳቤ ምክንያት የማንነት፣ ተሳትፎና የውክልና መብታቸው እየተጠበቀ አይደለም። ባለፉት ጥቂት አመታት እንዳየነው እንደዚህ አይነት ማህበረሰቦች አስከፊ ለሆነ ማንነት ላይ ላተኮረ ጥቃት ተጋልጠዋል።

**አራተኛ**፤ ከተሞች ፤ ብዙዎቹ በኢትዮጵያ የሚገኙ ከተሞች በተለይም በደቡብ፣ ምእራብና ምስራቅ ሕብረ-ብሔራዊ ቢሆኑም ባለቤት ተብለው እውቅና ከተሰጣቸው ማህበረሰቦች ውጭ ያሉት ዜጎች እውቅና ተሳትፎ የላቸውም። በሌላ አነጋገር ከተሞቹ

ሕብረ-ብሔራዊ ቢሆኑም አሳታፊ የሆነና የቋንቋና የባህል ብዝሃነትን የሚያንፀባርቅ አሰራር አልተዘረጋም፡፡ ይሄ ጉዳይ መፍትሔ ካልተሰጠው የግጭት መንሥኤ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 4. ማጠቃላያ

ከ1983ቱ የመንግስት ለውጥ በኋላ ወደ ሥልጣን የመጣው ኢሕአዴግ የብሔረሰብን/ማንነትን መሠረት ያደረገ የፌደራል ሥርዓት በመመስረት የብሔረሰቦችን እኩልነት በተግባር ለማዋል ሞክሯል፡፡ በተለይም በ1987ቱ ሕገ-መንግሥት  የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸው ያለገደብ እንዲተገበር በመደንገጉ ከቀደሙት የመንግሥት ሥርዓቶች ለየት ያለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶች በብሔር ማንነት ላይ ማጠንጠናቸው፣ ክልል የማቋቋምና የመገንጠል መብት ያለገደብ መፈቀዳቸውና  መሬት ላይ በሚታዩ የአተገባበር ችግሮች ምክንያት የፌደራል ሥርዓቱ ፈተና ገጥሞታል፡፡ የክልል እንሁን ጥያቄዎችና በብሔረሰቦችና በክልሎች መካከል በሚነሱ የድንበር ግጭቶች ፈታኝ ጉዳዮች እንደሆኑ ያለፉት 28 ዓመታት በአጠቃላይና (በተለይ ያለፉት 4 ዓመታት) ትልቅ ማሳያዎች ናቸው፡፡  የማንነት ጥያቄዎች፤ የድንበር ውዝግቦች፣ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች፣ የራስን ክልል ለማቋቋም የሚቀርቡ አቤቱታዎችና እነዚህን ጥያቄዎች ለመፍታት እየተሄደባቸው ያሉ መንገዶች ለፌደራል ሥርዓቱ ውጤታማ መሆንና አለመሆን ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በፌደራል ሥርዓቱ ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች በተገቢው መንገድ ለመመለስ የመንግስትን የመፈጸም አቅም ከማሳደግ በተጨማሪ አንዳንድ የሕገ-መንግስት ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ በክልል ምስረታ ዙሪያ ያለው ውዝግብ ያሳያል፡፡

## 5. የፖሊሲ ምክረ-ሃሳቦች

- ***የፌደራል አደረጃጀቱን መርሆዎች መፈተሽ***

የክልል ምስረታ ጥያቄን አወዛጋቢ የሚያደረገው፤ ሕገ መንግስቱ ለሁሉም ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እስከ መገንጠል ማስፈሩ እና የፌደራል አደረጃጀቱ

መልካዓ-ምድርንና ማንነትን ማጣመሩ ነው። በመሆኑም የፌደራል ሥርዓቱ ብሔርተኝነትን ከማራመዱም በላይ በብሔረሰብ ማንነት ላይ በተመሠረቱት ክልሎች መካከል ክፍ ያለ የሚዛን ልዩነት አለ። በቁጥር ከፍ ላሉት ብሔረሰቦች ክልል ሰጥቶ የሌሎቹን መከልከል አወዛጋቢነቱ እንዲቀጥል እንደሚያደርግ መረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም የብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ባከበረ መልኩ የፌደራል ሥርዓቱን የአደረጃጀት መርሆዎች መከለስ አስፈላጊ ነው።

### *የብሔርና የባህል ብዝሃነትን በክልሎች ማራመድ*

የራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ ለመመለስ በሚያስቸግር ሁኔታ እንዲስፋፉ ያደረገው በሕገ-መንግስቱ የተደነገገው የብሔር ማንነትና ግዛትን (መሬትን) የሚያቆራኘው የመንግስት አደረጃጀት መርህ ነው። ይህ መርህ ለብሔረተኝነት መጠናከር አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ሕብረ-ብሔራዊነትን መገንባት አስቸጋሪ አድርጎታል። ራስን በራስ በማስተዳደር በኩል የተለየ ማንነት ያላቸው ወገኖች ባሉበት ክልል ሆነው መብታቸው እንዲከበር ከመጠየቅ ይልቅ የብሔረሰብ ማንነትን ወደሚጋሩበት ክልል (ዞን) እንዲሄዱ ይገፋፋቸዋል። እንዲህ አይነቱ ጥያቄ አጨቃጫቂ ከመሆን አልፎ የግጭት መንስኤ እየሆነ ነው። በመሆኑም የፌደራሉና የክልል ሕገ-መንግስቶች የብሔርና የባህል ብዝሃነትን እንዲያራምዱ ለማድረግ የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል። ማሻሻያዎቹ የአናሳ ማህበረሰቦች መብቶችን በክልሎች ውስጥ በማስጠበቅ ከክልል ወጥተን የራሳችንን ክልል እናቋቁም ወይም ወሰን ይቀየር የሚሉ ጥያቄዎችን ሊቀንስ ከመቻሉም በላይ ብዝሃነትን ያከበረ ሕብረ-ብሔራዊ አንድነትን ያጎለብታል።

- ***በአዲስ ክልል የማቋቋም ሂደት የፌደራልና የክልል መንግስታት ሚና እንዲኖራቸውማድረግ***

በፌደራሉ ሕገ-መንግስት ድንጋጌዎች መሠረት አዲስ ክልል (ወይም ከክልል ደረጃ በታች) ያለ መዋቅር የማቋቋም ጥያቄ ለጠያቂው ቡድን/ብሔረሰብ ብቻ የተተወ ነው። በተጨማሪም ጠያቂው አካል ምንም ዓይነት ምክንያት ማቅረብ የማይጠበቅበት መሆኑና የአካሄድ ሥርዓቱም እጅግ ቀላል በመሆኑ ሁሉም ብሄረሰቦች በሚባል ሁኔታ የክልልነት ጥያቄ ማቅረባቸው የማይቀር ያደርገዋል። የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮንም እንደገመገምነው አንድ ብሔረሰብ ተገንጥሎ የራሱን ክልል ለማቋቋም የሚያካሂደው እንቅስቃሴ የራሱን መብት ለማስጠበቅና ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ቢሆንም ሂደቱና ውጤቱ ግን የሚገነጠልበትን ክልል ህዝብና የፌደራል

መንግሥቱንም እንዲሁም ጠቅላላ ሀገሪቱን የሚመለከት ጉዳይ ነው። ስለዚህም የፌደራል መንግስቱና ጥያቄው የቀረበበት ክልል ሂደቱን ከማስፈፀም የዘለለ የውሳኔ ሰጭነት ሚና ሊኖራቸው ይገባል። ይህ መሆኑ ጠያቂውን ቡድን/ብሄር ወደ ድርድር እንዲመጣ ሊያደርገው ስለሚችል አዲስ በሚቋቋመው ክልል ውስጥ ለሚኖሩ አናሳ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተሻለ ከለላ እንዲሰጣቸው ያስችላል። ስለዚህም የሌሎች አገሮችን ልምዶችና የኢትዮጵያን ልምድ በመቀመር የሕገ መንግስቱ አንቀጾች ሊፈተሹና ሊሻሻሉ ይገባል።

- ***የራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች የሚመለከት ነጻ የሆነ ተቋም ማቋቋም***

አሁን ባለው ሕገ-መንግሥት ውስጥ ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮችን በባላይነት የሚከታተለው የፌደሬሽን ምክር ቤት ነው። ይሁን እንጂ ምክር ቤቱ ገለልተኛ ያልሆነ የፖለቲካ አካል ነው። በመሆኑም ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ በማድረግ ራስን በራስ በማስተዳደር ዙሪያ ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ የሚሰጥ ተቋም ማቋቋም ወይም ደግሞ ይሄን ተግባር ለጠቅላይ ፍርድ ቤት መስጠት አስፈላጊ ነው።

- ***ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ልዩ ወረዳዎች የሚቋቋሙባቸው መስፈርቶችን ማውጣት***

ሕገ-መንግስቱ ለብሔር/ብሔረሰቦች ክልሎችን የመመሥረት መብት ቢሰጥም ሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ይሄን መብት ማግኘት አይችሉም። በመሆኑም የተለያዩ ራስን በራስ የማስተዳደር መዋቅሮችን ለማቋቋም የሚያስችሉ መስፈርቶችን ማውጣት ተገቢ ነው። የእንዲህ አይነቱ መስፈርት መውጣት የክልልና የሌሎች መዋቅር ጥያቄዎችን ለመቀነስ ይረዳል።

- ***ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት***

የመንግሥት አካላት ከሕብረተሰቡ ለሚቀርቡ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎችን ሲያስተናገዱ የቆዩበት መንገድ ተገቢውን ምላሽ ያለመስጠትና ለማፈን መሞከር ናቸው። እነዚህ ተግባራት ግን ጥያቄዎችን ለጊዜው ከማዳፈን ውጭ መፍትሄ አያመጡም። በመሆኑም የመንግስት አካላት ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት የጠያቂውን ማህበረሰብ ችግሮች መረዳትና ለችግሮቹ መፍትሄ መስጠት አላስፈላጊ ግጭቶችን ለማስወገድ ከመጥቀሙም በላይ በፖለቲካ አመራሩና በማህበረሰቡ መካከል መተማመንን ይፈጥራል።

# II. በኢትዮጵያ ፌደሬሽን
# የክልል፤ዞን እና ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች እና የመፍትሄ ሃሳቦች

ኃይለየሱስ ታዬ

## 1. መግቢያ

በሃገራችን ኢትዮጵያ የሚነሱ ራስን በራስ የማስተዳደር ማለትም የተለያዩ ማህበረሰቦች በሚኖሩበት አካባቢ የጋራ ጉዳዮቻቸውን በራሳቸው የሚያከናውኑበትን እና እንደ ቡድን የቡድን መገለጫ የሆኑ ባህላቸውን፤ ቋንቋቸውን እና ሌሎች መገለጫዎቻቸውን በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል አውድ ለማግኘት የሚያቀርቡት ጥያቄ ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ እስከተፈጸመ እና የሌሎችን መብት እስከ አከበረ ድረስ የፌደራል ስርዓት ሁለት መሰረታዊ መርሆዎች ከሆኑት የራስ አስተዳደር እና የጋራ አስተዳደር አንዱ የሆነው የራስ አስተዳደር ተግባራዊነት መገለጫ አድርጎ መውሰድ ተገቢ ነው።

ፌደራላዊ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ ከተተገበረ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ህብረ-ብሔራዊ በሆኑ ሀገሮች ህብረ-ብሔራዊነት ጋር ተያይዘው ለሚኖሩ የፖለቲካ፤ ማህበራዊ፤ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች በአንጻራዊ መልኩ የተሻለ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል። ከነዚህ ምላሽ ከሚሰጥባቸው መንገዶች አንዱ የተለያዩ ከባቢዎች ያላቸውን ከባቢያዊ አቅም እና የከባቢውን ማህበረሰብ ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ ስራ ላይ በማዋል የከባቢያቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ እና ለጋራ ሀገራዊ ልማት የድርሻቸውን አስተዎጽኦ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠርን ይጠይቃል።

የፌደራል ስርዓት ሁለት ተፈላጊ ግን ተቃራኒ የሚመስሉ ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ስርዓት በመሆኑ ሁሌም ሚዛን መጠበቅን የሚጠይቅ ሲሆን ስርዓቱ ግን ውሥብስብ በመሆኑ ስርዓቱን ለመተግበር ለስርዓቱ መሠረት የሆኑ ተቋማትን ተቋማዊነት ከማጠናከር በማይተናነስ መልኩ ለስርዓቱ ውጤታማነት አጋዥ የሆኑ የስርዓቱን እሴቶች እና መርሆች የራስ ማድረግ እና መተግበርን ይጠይቃል።የአንድን ስርዓት ውጤታማነት የሚወስኑት ተቋማት እና ተዋናዮች ብቻ ሳይሆኑ ስርአቱን ለመተግበር አጋዥ የሆኑ እሴቶች፤ መርሆዎች እና አመለካከቶች ጭምር መሆናቸው ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግልጽ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው።

በሀገራችን ከፌደራሊዝም አስተሳሰብ እና ከፌደራላዊ ስርዓት ጋር ተያይዘው የሚታዩ ችግሮች ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎችን ጨምሮ የፌደራሊዝም ፍልስፍና እና የፌደራል ፖለቲካ ስርዓትን እሳቤዎች በአግባቡ ካለመገንዘብ የተነሳ፣ እሳቤውን በተሳሳተ መልኩ ማለትም ከመለያየት፤ ከመበታተን እና ከግጭት ጋር አያይዞ ማየት እንዲሁም ለሁሉም የሃገሪቱ ችግሮች የፌደራል ስርዓቱን የጦስ ዶሮ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ናቸው ቢባል የተሳሳተ እሳቤ አይሆንም::

ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በራሱ ችግር አይደለም:: እንዲያውም ተፈላጊና ጠቃሚ ነው:: ዋናው ጉዳይ አፈጻጸሙ ላይ ነባራዊ ሁኔታዎችን እና ራስን በራስ ማስተዳደር ማለት የብቻ አስተዳደር ማለት ሳይሆን በከባቢው ከሚኖሩ ሌሎች ማህበረሰቦች ጋርም አብሮ የመኖርን፣ በሀገር ደረጃ በጋራ አስተዳደር መሳተፍን እና አንድ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ የለማች ሀገር መገንባትንም ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ማድረግ ነው:: ፌደራሊዝም ከመነሻው አብሮ የመኖር ፍልስፍ ነው:: በዚህ ለውይይት መነሻ ፅሁፍ በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ተመስርቶ አጠቃላይ በሆነ መልኩ  በሀገራችን እየተነሱ ያሉ የአደረጃጀት ጥያቄዎች፤ ለጥያቄዎች መነሻ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች፤  ለጥያቄዎች መበራከት ገፊ የሆኑ አሁናዊ ምክንያቶች፤ ለጥያቄዎቹ ሀገራዊ ሁኔታዎችን መሠረት አድርጎ ምላሽ የመስጠት አስፈላጊነት እና ለቀጣይ ሊጠቅሙ የሚችሉ ምክረ ሃሳቦችን ባካተተ መልኩ ቀርቧል::

**2.የህግ ማዕቀፎች**

በፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በየደረጃው ለሚቀርቡ የአደረጃጀት ጥያቄዎች ዋናው የህግ ማዕቀፍ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት ሲሆን የሕገ-መንግስቱ የተለያዩ አንቀጾች በግልጽ በቀጥታም ሆነ የአንቀጾችን ውስጣዊ ይዘት በመፈተሽ መረዳት እንደሚቻለው፣ በፌደራል ስርዓቱ ውስጥ በተለያየ እርከን የሚገኙ መንግስታዊ አደረጃጀቶች እንደሚኖሩ አስቀምጧል:: ከነዚህም አንቀጾች ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 1 ሀገሪቱ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አወቃቀር እንደምትከተል የሚደነግግ መሆኑ ፌደራላዊ አደረጃጀት ቢያንስ ሁለት መንግስታት መኖርን መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ እና ይህ አንቀጽ የፌደራል መንግስት እና የክልል መንግስታት መኖርን የሚያመላክት ስለሆነ ለክልሎች አደረጃጀት መኖር እንደ መነሻ አንቀጽ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::
2. አንቀፅ 39/ 3 ማንኛውም የኢትዮጵያ ብ/ብ/ህ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው:: ይህ መብት ብ/ብ/ህ በሰፈረበት መልከአምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማትን የማቋቋም፣ በክልል እና በፌደራል አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ

ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል። ይህ አንቀጽ በየደረጃው ብ/ብ/ህ መሰረት ያደረገ ልዩ ዞን ፤ልዩ ወረዳን የማደራጀት ጥያቄ የሚያቅፍ የህግ ማዕቀፍ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

3. አንቀጽ 47/2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱ ክልሎች ውስጥ የተካተቱ ብ/ብ/ህ በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው።ይህ አንቀጽ ብ/ብ/ህ በአንቀጽ 47/3 የተቀመጠውን ሂደት ተከትለው የራሳቸውን ክልል መመስረት እንደሚችሉ ያስቀመጠ ሲሆን ይህም አንቀጽ በክልል ደረጃ ራሳችንን ማደራጀት አለብን ለሚሉ ብ/ብ/ህዝቦች ጥያቄ መሰረት የሆነ ሕገ-መንግስታዊ ማዕቀፍ ነው።
4. አንቀጽ 50/4 ክልሎች በክልልነት እና ክልሎች አስፈላጊ ሆነው በሚያገኙዋቸው የአስተዳደር እርከኖች ይዋቀራሉ። ሕዝቡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ ይሳተፍ ዘንድ ለዝቅተኛ እርከኖች በቂ ስልጣን ይሰጣል። ይህ አንቀጽ በቂ ስልጣን ያላቸው ዝቅተኛ የመንግስት እርከኖች በክልሎች ይሁንታ መደራጀት እንዳለባቸው ጠቋሚ ሕገ-መንግስታዊ ማዕቀፍ ሲሆን በክልሎች ለሚቀርቡ የአደረጃጀት ጥያቄዎች እንደ ህጋዊ ማዕቀፍ ሊያገለግል ይችላል።
5. አንቀጽ 88 ፖለቲካ-ነክ አላማዎች

1/ መንግስት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት። ይህ አንቀጽ በሁሉም እርከኖች ለሚኖሩ ራስን በራስ የማስተዳደር ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ጥያቄ ለማቅረብ የህግ ማዕቀፍ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

በየክልሉ ሕገ-መንግስቶች ስለ ዞን፤ ወረዳናቀበሌ አደረጃጀቶች የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት ከላይ የተዘረዘሩት አንቀጾች በየጊዜው ለሚቀርቡ የአደረጃጀት ጥያቄዎች መሰረታዊ የህግ ማዕቀፎች ናቸው።

### 3. በአሁኑ ወቅት ለጥያቄዎች መበራከት ገፊ ምክንያቶች

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርዓት የአደረጃጀት ጥያቄዎች ፌደራላዊ ስርዓቱ ከተመሰረተ ጀምሮ ይቀርቡ የነበሩ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ለጥያቄዎቹ መበራከት የሚከተሉትን ጉዳዩች እንደ ገፊ ምክንያቶች መወሰድ ይቻላል።

1. በሃገሪቱ ከተፈጠረው የለውጥ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ እና ማህበረሰቡን በሚመሩ ልሂቃን ውስጥ “ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ ያሉ ጥያቄዎቻችን ማስፈጸም የሚቻልበት የፖለቲካ ምህዳር ተፈጥሯል” የሚል አስተሳሰብ መያዝ እና በተጨባጭም ለቆዩ የአደረጃት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት መጀመሩ ( ለምሳሌ የሲዳማ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል፤ በተለያዩ ክልሎች የተፈቀዱ የዞኖችና ወረዳዎች አደረጃጀቶች)፣
2. በፌደራል ስርዓት ስልጣን ያልተማከለ እና በየደረጃው የሚኖር የስልጣን ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚታዩ የስርዓቱ ባህሪያት እና የአደረጃጀት ጥያቄዎችን ለማንሳት መሰረት የሚሆኑ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች መኖር ከለውጥ እንቅስቃሴው ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ እና ማህበረሰቡን በሚመሩ ልሂቃን የአደረጃጀት ጥያቄ ማቅረብ ሕገ-መንግስታዊ መብት ነው:: ይህም መተግበር አለበት የሚል እንቅስቃሴ መኖር ( ለምሳሌ የጉራጌ ዞን የ”ክልል እንሁን” ጥያቄ)፣
3. የእኩል ተጠቃሚነት ዕድል ጥያቄዎች ፤ “አድሎአዊነት አለ” ከሚል ስሜት የተነሳ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ “ማደግ የምንችለው የራሳችን ክልል፤ ዞን እና ወረዳ ሲኖረን ነው” የሚል አስተሳሰብ መያዝ ( ለምሳሌ በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በ2011 የተደረገው ጥናት ጎልቶ የወጣ መሆኑ)፤ የለውጡም እንቅስቃሴ አንዱ መነሻ እኩል ተጠቃሚነት ዕድል የለም የሚል መሆኑ፣
4. “በነባሩ መዋቅር ተገቢውን አገልግሎት አላገኘንም ፤ ያለው መዋቅርም የአካታችነት ችግር አለበት” የሚሉ እሳቤዎች፣
5. የማንነት ጥያቄዎች እየጎሉ መምጣት እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ውድድር የሚመስሉ አካሄዶች መኖር፣
6. የፓለቲካ ልሂቃኑ “ተጠቃሚ እንሆናለን” የሚል እሳቤ::

በሀገሪቱ ለሚታዩ የአደረጃት ጥያቄዎች ከስርዓተ-ባህሪ፤ የህግ ማዕቀፎች እና ከሚታዩ የለውጥ እንቅስቃሴዎች እና ከነባር አደረጃጀቶች የአሰራር ክፍተቶች ጋር ተያይዞ ከላይ የተዘረዘሩትን ገፊ ምክንያቶች ማስቀመጥ ቢቻልም ጉዳዩ የተመረጡ አብነቶችን/ኬዞችን መሠረት አድርጎ በጥልቀት ማጥናትን የሚጠይቅ መሆኑን ገልጾ ማለፍ ተገቢ ነው::

## 4. ለሚነሱ ጥያቄዎች አሁናዊ እና ሃገራዊ ተጨባጭ ሁኔታን መሠረት ያደረገ ምላሽ መስጠት አስፈላጊነት

አደረጃጀቶች በህዝብ ውስጥ የሚፈጠሩ የማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ባህላዊ እንዲሁም የዴሞክራሲ እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዲፈቱ የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው:: በፌደራል ስርዓት የአደረጃጀት ጉዳዮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሚባል ደረጃ የሚጠናቀቁ ሳይሆን በሃገሪቱ ያለውን ለውጥ እና የማህበረሰቡን ፍላጎቶች መሠረት አድረጎ በየጊዜው መስተናገድ ያለባቸው መሆኑን የብዙ ፌደራል ሃገራት ተሞክሮ ያሳያል (ለምሳሌ ናይጀሪያ፤ ህንድ፤ ሲዊዘርላንድ፤ ቤልጂም፤ ጀርመን):: በሀገራችንም ቢሆን በተለያዩ ክልሎች የዞንና የወረዳ ጥያቄዎች መልስ እያገኙ የመጡበት ሁኔታ ያለ መሆኑ ይታወቃል:: መረጃዎች እንደሚያመላክቱት አሁን በሃገራችን ያለው የክልላዊ መንግስታት አደረጃጀት፣

በ 11 ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት፣

በ 2 ለፌደራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ ቻርተርድ የከተማ አስተዳደሮች፣

በ 68 ዞኖች፣

በ 832 የወረዳ አስተዳደሮች፣

-እስከ ቅርብ ባለ መረጃ ልዩ ወረዳ በ5 ክልሎች ብቻ የሚገኝ 13 ወረዳዎችን የሚያካትት አደረጃጀት ነው::

እነርሱም ደ/ብ.ብ/ህዝቦች ------ 8፣

ቤንሻንጉል ጉምዝ ---------2፣

አፋር ----------1፣

ጋምቤላ -----------1፣

አማራ -----------1::

በ 22805 ቀበሌ አስተዳደሮች፤ - የከተማ 1656፣

- የገጠር 21149፣

- በ116 የከተማ አስተዳደሮች

የተዋቀረ ሲሆን እነዚህ የአስተዳደር እርከኖች 123,379,924 (የተመድ 2021 ትንበያ) ህዝብ መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ በቂ ናቸው ተብሎ ካለመገመቱም በላይ የፌደራል ስርዓት ሊያስገኙዋቸው የሚገቡ ጥቅሞችን ያሳካሉ ተብሎ አይገመትም፡፡

የፌደራል ስርዓት ከሚያስገኛቸው ብዙ ጥቅሞች ውስጥ በተወሰነ መልኩ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል

-ብዙ ማዕከሎች መፍጠር፣

-ድርብ የስልጣን ክፍፍል፣

-ብዝሃነትን እና አንድነትን አጣምሮ ማስተናገድ፣

- ሁሉንም ፍላጎቶች አመዛዝኖ አንጻራዊ በሆነ እና በተሻለ መልኩ ማስተናገድ፣
- ከባቢያዊ የመልማት አቅም እና ፍላጎትን ከሀገራዊ የመልማት አቅም እና ፍላጎት ጋር አስተሳስሮ የህዝቡን በልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

-ትንሽ ሀገር ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚኖሩ ውስንነቶችን በመቅረፍ እና ዕድሎችን በማጎልበት ትልቅ ሃገር ከመሆን ጋር የሚገኙ ዕድሎችን ማጎልበት እንዲሁም ውስንነቶችን መቅረፍ፣

-የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ ( እንደ ሃገር፤ክልል፤ወረዳ ፤ቀበሌ)፣

- - ፎረም ሾፒንግ፣
- ሰፊ ገበያ መፍጠር፣
- ኢኮኖሚ ኦፍ ስኬል
- ጠንካራ እና ተሰሚ የሆነች ትልቅ ሃገርን መፍጠር፡፡

በመሆኑም በሀገራችን እነዚህን ጥቅሞች ለማረጋገጥ እና በማህበረሰቡ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተጠና መልኩ ወቅታዊ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ምክረ ሀሳቦች በሚቀጠለው ክፍል ቀርበዋል፡፡

## 5. ለወደፊት ምክረ-ሃሳቦች

በፌደራላዊ ስርዓቶች በየጊዜው የሚኖሩ፤ ሀገራዊ እና ከባቢያዊ ማህበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊ ለውጦች እና የፌደራል ስርዓቱ አንዱ መርሆ የሆነውን የራስ አስዳደርን መሰረት አድርጎ የአደረጃጀት ጥያቄዎች በየጊዜው መነሳታቸው የማይቀር መሆኑን ግንዛቤ በማስገባት ለተግባራዊነቱ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ከዚህ የሚከተሉት ምክረ-ሃሳቦች ቀርበዋል፤

1. በሀገራችን የነበረው እና አሁንም እየቀጠለ ያለው የክልሎች አወቃቀር ሁለቱንም (ማለትም፤ አንድ ብሄርን መሰረት ያደረገ እና የተለያዩ ብሄሮች የታቀፉበት ክላስተር) መሰረት ያደረገ መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም እንደ ተጨባጭ ሁኔታው ሁለቱንም አዋህዶ (ብሄርና ክላስተርን) መጠቀም የተሻለ አማራጭ እንደሚሆን ይመከራል። ከሀገሪቱ የብሄር ስብጥር እና አቀማመጥ አንድ እና ያው ብቻ አወቃቀር ይዞ መሄድ የማህበረሰቡን ችግር ካለመፍታቱም በተጨማሪ የአካባቢዎችን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆን ስለማያስችል፣

- በክላስተር የተደራጁ ብሄሮች ከብሄር ጋር ተያይዘው የሚነሱ
- የባህል፤የታሪክ እና የቋንቋ ጉዳዮች በልዩ ዞንና ፤ወረዳ ማስተናገድ
- በክልል ደረጃ ኮንሶንሴሽናል ቅርጽ ያለው አስተዳዳር መመስረት
- ብዙ ማዕከሎች ያሉት ክልል መፍጠር፣
- በክልሉ ለሚኖሩ ብ/ብሄ/ህዝቦች እኩል የመልማት ዕድል መፍጠር፣
- ህብረተሰቡን ማሳተፍ እና የመፍትሄ አካል በማድረግ ችግሮቹን ማቃለል ይቻላል።

2. አንቀጽ 47/2 መብት ቢሆንም መብቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን የአሰራር ስርዓት የሚደነገግበትን መንገድ ማመቻቸት፣

3. ህብረተሰቡን በቅርበት አገልግሎት የሚሰጡ ጠንካራ አደረጃጀቶችን መፍጠር ለምሳሌ የድጎማ/የሳብሲዲያሪነት መርህን ስራ ላይ ማዋል፣

4. የእኩል ተጠቃሚነት ዕድል መፍጠር፣

5. በክልል መንግስታት መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር፣

6. በህብረ ብሔራዊ ፌደራላዊ ስርዓት ማዕቀፍ ሀገራዊ አንድነትን ማጠናከር፣

7. በአዋሳኝ አካባቢ ለሚኖረው ማህበረሰብ መንግስታዊ አገልግሎቶችን በጋራ መስጠት፤

8. የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በየጊዜው የፌደራል ሥርዓቱን በሚያጠናክር መልኩ እየፈቱ መሄድ፣

9. በየክልሉ ተበታትነው የሚኖሩ ዜጎችን ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፣

10. መደጋገፍ እና በጋራ መልማት፣

11. የግልና የጋራ ኃላፊነት/ሥልጣንን አጣጥሞ እና ሚዛን ጠብቆ ማስኬድ

12. በፌደራሊዝም፤ ፌደራላዊ ስርዓት ሕገ-መንግስት እና ሕገ-መንግስታዊነት ዙሪያ

    ሰፊ የአመለካከት እና የአስተሳሰብ ግንባታ ስራዎችን ማከናወን

13. ህብረ-ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ የጋራ ማንነትን ማጠናከር

በተለያዩ እርከኖች የሚቀርቡ የራስ በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች ፌደራል ስርዓቱን በሚያጠናክር እና ስርዓቱን ሰላማዊና የተረጋጋ በሆነ መልኩ ለመመለስ፣ ጥያቄውን ለማቅረብ ገፊ የሆነ ምክንያቶችን ለመቀነስ ከላይ የተዘረዘሩትን ሃሳቦች ግንዛቤ ያስገባ ተግባር ማከናወን ጠቃሚ ይሆናል።

## 6.ማጠቃለያ

የአደረጃጀት ለውጦች የፌደራል ሥርዓት በሚከተሉ ሃገራት አይቀሬ ሲሆን የአተገባበሩ ሁኔታ እንደየ ፌደሬሽኖቹ አፈጣጠር፤ ባህሪ እና ነባራዊ የፖለቲካ፤ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እንደሚለያይ ይታወቃል። ስለሆነም በየጊዜው በጥናት እየለዩ የራስ አስተዳደርን እና ሀገራዊ አንድነትን በሚያጠናክር መልኩ መተግበር እና ለዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ጠንካራ እና የተሟላ አደረጃጀት በመፍጠር በማህበረሰቡ ከመንግስት አገልግሎቶች አሰጣጥ፤ ከልማት እና መልካም አስተዳደር እንዲሁም ከእኩል ተጠቃሚነት ዕድል ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥያቄዎችን በየጊዜው እየፈቱ መሄድ ያስችላል። ይህ በአደረጃጀት ጥያቄዎች  እና የመፍተሄ ሃሳቦች ዙሪያ የቀረበ የውይይት መነሻ ጽሁፍ በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ሃሳቦች ቀርበው የሰላ ውይይት በማድረግ በውይይቱ የተደረሰባቸው ነጥቦች ተለይተው በቀጣይ አብነትን/ኬዝን መሰረት ያደረገ ጥልቅ ጥናት ለማድረግ እና ለመንግስትም ምክረ ሃሳቦችን ለማቅረብ ጠቃሚ ይሆናል።

## 7.ማጣቀሻ መረጃዎች


- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህግመንግስት፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ አንደኛ ዓመት እትም ቁጥር 1, ነሐሴ 15 1987, አዲስ አበባ.

ኃይለየሱስ ታዬ

- የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል አደረጃጀት ጥያቄዎች መንስኤና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት. ሃምሌ 2011, አዲስ አበባ (ያልታተመ)

# III. አለመተማመን እና የመዋቅር ጥያቄ በኢትዮጵያ

ገብሬ ይንቲሶ ደኮ

## 1. መግቢያ፡- የመዋቅር ጥያቄ አረዳድ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ክልል፣ ዞንና፣ ወረዳ የመሆን ጥያቄዎች ይቀርባሉ፡፡ ይህንን ክስተት አስመልክቶ ሁለት ዓይነት አቋሞች ይንፀባረቃሉ፡፡ አንደኛው አቋም “የመዋቅር ጥያቄ የመልማት ጥያቄና ሕገ-መንግስታዊ መብት ስለሆነ አዎንታዊ ምላሽ ይገባዋል” የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው አቋም ደግሞ “ብሔር-ተኮር የአደረጃጀት ጥያቄ በልሂቃን የሚዘወር፣ ወደ ግጭትና መበታተን የሚያመራ የጠባብነት መገለጫ ስለሆነ መበረታታት የለበትም” የሚል ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ አንዱን ወይም ሌላውን አቋም በመደገፍ ወይም በመቃወም ከመከራከር ይልቅ የአደረጃጀት ጥያቄዎችን መሰረታዊ ምክንያት በመረዳት አውዳዊ ትንታኔ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

በቡድኖች መካከል ሃብትና ስልጣንን ለመቆጣጠር የሚደረግ የተለመደ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከወትሮ በተለየ ሁኔታ ዛሬ የመዋቅር ጥያቄ የሚነሳበት ምክንያት በአገሪቱ አለመተማመን (mistrust) በእጅጉ እየሰፋ በመምጣቱ ነው፡፡ በገቢርና በትርክት የሚገለጹ የአለመተማመን መንስኤዎች በርካታ ናቸው፡፡ አለመተማመንን ከአስቻይ ሁኔታዎች ጋር በመጣመር የመዋቅር ጥያቄዎች እንዲበራከቱ አድርጓል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አለመተማመን ሲሰፍን የግንኙነት መናጋት፣ የትብብር መቋረጥ፣ የሰላም መደፍረስና የልማት ሂደት መስተጓጎል የሚያስከትል መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ (Carey, 2017)፡፡

የአለመተማመንን ጉዳት ለመረዳት የመተማመንን (trust) ፋይዳ ማወቅ ይረዳል፡፡ እንደ ተማራማሪዎች አገላለጽ ከሆነ የመተማመን ጠቀሜታዎች ማህበረሰብን ማስተሳሰር (Coleman, 1988; Simmel, 1950)፣ ስርዓት ማስከበር (Parsons, 1937)፣ ትብብርን ማሳካት (Arrow, 1974)፣ ኢኮኖያዊና ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ መስተጋብሮችን ማቀላጠፍ (Coleman, 1988)፣ ዲሞክራሲያዊ መስተዳደርን ማረጋገጥ (Paxton 2002) እና የኢኮኖሚ ልማት (Fukuyama, 1995) ናቸው፡፡ ማቲው ኬሪም እንደዚሁ መተማመን ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራል፣ የወንጀል ድርጊት ይቀንሳል፣ ደስታን ያጐናጽፋል፣ ልማት ያሳልጣል፣ ብልጽግና ያመጣል እንዲሁም የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል (Carey, 2017) ይላል፡፡

በአንፃሩ፣ (Carey, 2017) የአለመተማመንን አፍራሽነት እንደሚከተለው ያብራራል፤ “በመተማመን የተገነባውን ግንኙነት አለመተማመን ያፈርሰዋል፡፡ መተማመን ሃብት ለማፍራት ሲረዳ አለመተማመን ለድህነት ይዳርጋል፡፡ መተማመን ተግባቦትና መቀራረብን ሲፈጥር

አለመተማመን ወደ መለያየት ያመራል" ብሏል። ኤድዋርድ ባንፊልድ የሚባል ተመራማሪ ደግሞ ከስልሳ ዓመት በፊት ያጠናቸውና ሜዲተራንያን ባህር አቅራቢያ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ውስጥ ስር የሰደደ አለመተማመን በመኖሩ ምክንያት ውሸት፣ ሐሜትና መካካድ እንዴት ከአስከፊ የኃላቀርነትና የድህነት አዙሪት እንዳይወጡ አድርጎ ቆልፎ እንዳስቀራቸው ያስረዳል (Banfield, 1958)። ማቲው ኬሪ አፍሪካዊትዋ ሞሮኮ ውስጥ ጥናት አድርጎ ከባንፊልድ ግኝት ጋር ተመሳሳይነት ያለው የአለመተማመን ድርጊትና ባህሪ እንዳስተዋለ ይገልጻል (Carey, 2017) ።

በህዝብና በተለያየ የመንግስት መዋቅር መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ መዋቅሩ አድሏዊነትንና ኢ-ፍትሐዊነትን የሚፈቅድ ከሆነ ተበደልን የሚሉ ዜጐችና ቡድኖች በስርዓቱ ላይ ዕምነት ያጣሉ።አለመተማመን ሲሰፍን ስጋት ያደረባቸው ወገኖች ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ ግንኙነትና ትብብር ማቆምና ነባሩን መስተጋብር የሚተካ አዲስ ግንኙነትና ስርዓት ማማተር ይጀምራሉ። በቀድሞ የደቡብ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል (ደቡብ ክልል) የተስተዋሉት የመዋቅር ጥያቄዎች መነሻቸው አለመተማመን መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል። በሌላ አባባል አንድ የአደረጃጀት መዋቅር መተማመን/ን በአግባቡ የሚያሰፍን ከሆነ የጋራ ተጠቃሚነትን አጠናክሮ አብሮ የመቀጠል ፍላጎት ስለሚጨምር የመዋቅር ጥያቄ የሚነሳበት ምክንያት ዝቅተኛ ይሆናል።

ስለዚህ እየተሸረሸረ የሚገኘውን የመተማመን ዕሴት የማስፈን ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የመዋቅር ጥያቄ መበራከት በአብነት የሚጠቀስ አንዱ የአለመተማመን ችግር ውጤት እንጂ ብቸኛው መገለጫ አይደለም። አለመተማመን ዘርፈ-ብዙ መገለጫዎች ያሉት ትልቅ አገራዊ አደጋ ሆኗል። ዛሬ አብሮአደግ ጓደኞሞች፣ በፍቅር የኖሩ ጎረቤታሞች፣ የአንድ ተቋም ባልደረቦች፣ የአንድ እድር አባላት፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ብሔረሰቦች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ወዘተ የማይተማመኑበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። እንደ ዜጋ፣ እንደ ህዝብና እንደ አገር ይህንን እውነታ ተቀብሎ ሳይዘገይ መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል።

2. የመዋቅር ጥያቄ መንስኤዎች በደቡብ ክልል

የቀድሞ የደቡብ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልልና መሪ ድርጅቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን) የአደረጃጀት ጥያቄዎችን መንስኤ ለማወቅና መፍትሔ ለማፈላለግ በምሁራን አንድ ሳይንሳዊ ጥናት አስጠንቶ ነበር። በዚህ ለህዝብ ይፋ በተደረገ ጥናት ግኝት መሰረት የብዙዎቹ የመዋቅር ጥያቄዎች ምክንያቶች አድሏዊነትና ኢፍትሐዊነት፣ የህግ የበላይነት አለመረጋገጥ፣ የደህንነት ስጋት፣ ቡድንተኝነትና የጥቅም ትስስር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ድክመት፣ የመሰረተ-ልማት ዕጥረት/ዕጦት እና የፖለቲካ ልሂቃን ቅስቀሳ ናቸው። የጥያቄዎቹ መነሻ አለመተማመን ስለመሆናቸው ከታች ቀርቧል።

የበጀት አጠቃቀም፣ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታና የትላልቅ ፕሮጀክቶች ስርጭት ፍትሐዊ እንዳልነበረ ተነስቷል። የክልሉ የበጀት ድልድል በተለይም የመጠባበቂያ በጀት አጠቃቀም የግልፅነት ችግር የነበረበት መሆኑ፣ የፌዴራል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ስርጭት የጋራ ተጠቃሚነትን ያለማረጋገጡ፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ፍትሐዊ አለመሆኑ እና ከሐዋሳ ከተማ በስተቀር ሌሎች ከተሞች እንዲያድጉ ክልሉ አለመደገፉ በቀድሞው የደቡብ ክልል ላይ እምነት ካሳጡት ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶች ናቸው። ክልሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በመተግበር አመርቂ ዕድገት ያስመዝገበ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሱት ኢ-ፍትሐዊ አሰራራሮች ምክንያት ዕድገቱ ያልተመጣጠነና በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ የታጠረ መሆኑ ያስከፋቸው ሌሎች አካባቢዎች እንዳሉ ጥናቱ አሳይቷል።

የክልሉ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ፍትሃዊነት፣ ጥራትና ቅልጥፍና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ ሁሉንም የክልሉ ህዝቦች በእኩልነት የማያይ እየሆነ መምጣቱም ተነስቷል። የፍትህ ስርዓት መዛባት፣ አድሏዊ አሰራር መኖርና እነዚህን ተቆጣጥሮ ስርዓት ማስያዝ አለመቻሉ እንደ አንድ ማሳያ ይጠቀሳል። ባለሙያዎች ከየዞኑና ከልዩ ወረዳዎች ወደ ክልል መስሪያ ቤቶች የሚመደቡት ወይም የሚዛወሩት በሙያ ብቃትና በታወቀ መስፈርት ሳይሆን በጥቅምና በወገንተኝነት በመሳሳብ እንደነበረ ይነሳል። አድሏዊነትና ኢ-ፍትሐዊነት እንደ ሥርዓት ተዘርግቶ ባለሥልጣናት እንዳሻቸው ያለተጠያቂነት ሲሰሩ ይህንን ለመቆጣጠር ክልሉ ዓቅምና ፍላጎት ማጣቱ የህዝቡን እምነት እንዳሳጣው ይገለጻል።

በክልሉ ያለው የስልጣን ክፍፍል ኢ-ፍትሐዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሀብትን በሚወስኑ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች የተቀመጡ ግለሰቦች ሥልጣናቸውን ለግልና ለቡድን ጥቅም ማዋላቸው ይጠቀሳል። በፌደራልም ይሁን በክልል ደረጃ ባሉ የሥልጣን ውክልና ቦታዎች ከተወሰኑ ቡድኖችና አካባቢዎች የመጡ ባለስልጣናት ብቻ እየተፈራረቁ ስልጣን የሚይዙበትና በሌሎች ቡድኖችና አካባቢዎች ላይ የበላይ የሆኑበት ሥርዓት ተፈጥሮ እንደነበርና ይህም "ተገፋን" በሚሉ ወገኖች ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ከማስከተሉም ባሻገር በክልሉ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ማድረጉ ይወሳል።

የደቡብ ክልል መንግስት የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥና የህዝቡን ደህንነት ለማስጠበቅ አለመቻሉና በህብረ-ብሔራዊነቱ የተደነቀ ክልል ብዝሃነትን ያስተናገደበት መንገድ ክፍተት እንደነበረው ተመልክቷል። በአንዳንድ አካባቢዎች ጥቃቶች ሲፈጸሙ ክልሉ ቀድሞ ደርሶ ህዝቡን ከመታደግ አንጻር ዳተኛ ወይም ደካማ ስለነበር ተጎጂዎች የመገለል ስሜት እንደተሰማቸው ይገለጻል። ሰዎች በማንነታቸው ምክንያት እየተጠቁ የክልል መስተዳድሩ ተደራሽ አለመሆን የባለቤትነት ስሜት ማጣት ተደርጎ ተወስዷል። በተለያዩ ምክንያቶች ተገምግመው ከሥልጣናቸው የተነሱ፣ የህዝብ ሀብት ያባከኑና የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈጸሙ የአመራር አባላት በህግ መጠየቅ ሲገባቸው ቡድናዊ ከለላ እየተደረገላቸውና ወደ ሌላ ቦታ የስራ

ምደባ እንዲሰጣቸው እየተደረገ ተጠያቂነት ስለጠፋ ስርዓተ-አልበኝነት መንገሱ ይነሳል። በአጠቃላይም በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር መዋቅሮች የሚፈጸሙ በደሎችን መርምሮ መቅጣት የሚያስችል ስርዓት በመጥፋቱ ህዝቡ እንደተማረረ ይወሳል።

የደቡብ ክልል በርካታ ብሔረሰቦችን ያቀፈ ቢሆንም በክልል ደረጃ ቡድንተኝነትና የጥቅም ትስስር በመፈጠሩ የአስተዳደር መዋቅሩም ሆነ የድርጅቱ የፓርቲ ሥልጣን እርከኖች ፍትሐዊ የህዝብ ውክልና እንዳልነበራቸው ይገለጻል። የተወሰኑ አካላት በመካከላቸው የተለያዩ የጥቅም ግንኙነቶችን ፈጥረው ሌሎችን ስላገለሉ "በአግባቡ አልተወከልኩም" የሚሉ ድምጾች ወይም "ተገፍተናል" የሚሉ ዕሳቤዎች ተበራክተው የደቡብ ክልልን የአደረጃጀት አካታችነት ጥያቄ ውስጥ አስገብተውት ነበር። በማንነትና በጥቅም የተሳሰረው ቡድንተኝነት አግላይ ብቻ ሳይሆን ለህዝቡ የማይጠቅም መሆኑን አጥብቀው የሚከራከሩትንና የሚተቹትን አመራሮች እስከ ማግለል የሚያደርስ ጫና ይፈጠርባቸው እንደነበር ተጠቅሷል።

ከክልሉ የቆዳ ስፋት የመሠረተ ልማት አለመዘርጋት ጋር ተያይዞ ከክልሉ ማዕከል በርቀት የሚገኙ ዞኖች በጀታቸውን በትራንስፖርትና አበል ወጪ እንዲሁም የልማት ጊዜያቸውን በክልል ስብሰባዎችና ሥልጠናዎች እንደምያባክኑ ይወሳል። ወደ ክልል የሚያስኬድ ጉዳይ ያላቸው ሰዎችም ለወጪና ለእንግልት ይዳረጋሉ ተብሏል። እስካሁን ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ በሀገረ-መንግስት ግንባታ ሂደት ህዝባቸው እንደተገፋና የቀድሞ ታሪካቸው ተገቢው ቦታ እንዳልተሰጠው በመግለጽ ክልል የመሆን ጥያቄ ያነሱም ነበሩ።

በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔረሰቦች በሙሉ በጎሳ፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በታሪክ፣ በሃይማኖት፣ በጋብቻ፣ በኤኮኖሚና በሌሎች ሐረጎች የተጋመዱ ናቸው። ነገር ግን አንዳንድ አመራሮች የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት የብሔርተኝነት ዕሳቤን አክርረው በመስበክና አንዱ በሌላው ቡድን እንደተበደለ በማስመሰል በሰላምና በፍቅር ይኖሩ በነበሩ ህዝቦች መሃል አለመተማመንና ብሎም ግጭት እንዲፈጠር ማድረገቸውን ጥናቱ ይጠቁማል። እነዚህ ልሂቃን አንዳንድ ጊዜ ከባለሃብቶች ጋር በመመሳጠር ህዝቡን በመዘወር አዲስ መዋቅር ከተፈቀደ ስልጣን ለመያዝ፣ ከዚህ በፊት ለፈጠሯቸው ችግሮች ተጠያቂ ላለመሆን እና በህዝብ ሃብት ለመበልጸግ እንደሚመኙ ተመላክቷል።

በአጠቃላይ በቀድሞ የደቡብ ክልል የሚነሱት ክልል የመሆን ጥያቄዎች በዋናነት በነባሩ አደረጃጀት ላይ እምነት በማጣት ምክንያት ነበር። በተጨማሪም የክልል መዋቅር ያላቸው ህዝቦች አጠገብ ካሉ በዞን ከተደራጁ ህዝቦች አንፃር የተሻሉ እንደሆነም ተገልጿል። ለምሳሌ ያህል የጋምቤላ ክልልና የቀድሞ የቤንች ማጂ ዞን ህዝብ በተነጻጻሪ እኩል ሆነው የቤንች ማጂ ዞን ከደቡብ ክልል የሚያገኘው በጀት የጋምቤላ ክልል ከፌደራል ቀጥታ ከሚያገኘው በጀት እጅግ አነስተኛ ነው የሚል ግምገማ ነበር። አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ላላቸው ሐረሪ፣ አፋርና ቤኒሻንጉል-ጉምዝ ህዝቦች በክልል የመደራጀት መብት ያጎናጸፈው ሕገ-መንግስት ደቡብ አካባቢ

የበለጠ ቁጥር ያላቸው ህዝቦች ያቀረቡት የመብት ጥያቄ የሚከለከሉበት ምንም ምክንያት የለም የሚል ክርክር ይነሳል። ከዚህ አካሄድ ሕገ-መንግስቱ የመዋቅር ጥያቄ አስቻይ ሁኔታ እንደሆነ እንረዳለን።

## 3. የመዋቅር ጥያቄ አስቻይ ሁኔታዎች

### 3.1. የህግ አግባብ መኖር

በኢትዮጵያ የአስተዳደር መዋቅር ጥያቄ መበራከት አስቻይ ሁኔታዎችን ቢያንስ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው የፌደራሉ ሕገ-መንግስትና የክልል መንግስታት ሕጎች የመዋቅር አደረጃጀትን የሚፈቅዱ መሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው የመዋቅር ጥያቄን በቀላሉ ህዝባዊ ማድረግ የሚቻል መሆኑ ነው። በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 39/3 መሰረት "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል"። ክልሎችም የአስተዳደር መዋቅር አመሰራረትን የሚደነግጉ የሕገ-መንግስት አንቀፆችና ተጨማሪ ሕጎች አሏቸው። ለምሳሌ በደቡብ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51/3/ለ መሰረት አስፈላጊ ሲሆን የህዝብ ብዛትን፣ የቆዳ ስፋትና ገቢን ባገናዘበ የአስተዳደር እርከን ማቋቋም ይቻላል። ከዚህ አንቅፅ በተጨማሪ ክልሉ በ2011 ዓ.ም. ያስተላለፈው ውሳኔ የዞንና የወረዳ መዋቅር ለመጠየቅ መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ይዘረዝራል። በክልሉ የቅርብ ግዜ ታርክ ህጋዊ መስፈርቶችን አሟልተው አዲስ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ተቋቁመዋል።

### 3.2 የሰው ልጅ በተፈጥሮ ቡድንተኛ መሆን

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ለቡድንተኝነት አዝማሚያ አመቺ ነው። እንደሚታወቀው ሰዎች በተፈጥሮ ቡድንተኛና ወገንተኛ ናቸው። የጋራ መለያ ፈጥረው በአንድነት ስሜት በቡድን መኖር ይፈልጋሉ። ሰዎች ከሚካተቱባቸው የቡድን ዓይነቶች አንዱ ብሔረሰብ ሲሆን የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ደግሞ ለቡድን መብት ትኩረት ስለሚሰጥ ከቡድንተኝነት አዝማሚያ ጋር አይጋጭም። ሰዎች በቡድን መሰባሰባቸው አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች አሉት (Simon, 2002)። አዎንታዊ ገጽታው በግለሰብ ደረጃ በተናጠል የማይከናወኑ ተግባራትን በጋራ ለመወጣት የሚያስችል መሆኑ ሲሆን፣ አሉታዊ ገጽታው ደግሞ "እኛ" እና "እነሱ" የሚል ወገንተኝነት ስላለበት በቡድኖች መሃል ያለመግባባት ሲኖር እርስ በርስ ወደ መገፋፋትና መጎዳዳት የሚያመራ መሆኑ ነው።

ብሔረሰቦች የቡድን መለያዎች (ቋንቋ፣ ባህል፣ ስነልቦናዊ አንድነት፣ ታሪክ፣ ወዘተ) አላቸው። እያንዳንዱ ብሔረሰብ ባህሉን መጠቀምና ማሳደግ መብቱ ነው። በቀናነትና በወንድማማችነት ስሜት የአንዱን ብሔረሰብ ጠቃሚ የባህል ዕሴቶች በጋራ መጠቀምና ማሳደግ ለአብሮነት፣

ለሰላምና ለልማት እጅግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ባፈነገጠ መልኩ ሕገ-መንግስቱን የቡድንተኝነት አዝማሚያ እንዲጎለብት መጠቀም ግን በህዝቦች መሃል አለመተማመን እንዲፈጠር ያደርጋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ እርምት የሚፈልጉ አስተሳሰቦች አሉ። የራስን ባህል የተሻለ አድርጎ ለሌሎች ዝቅተኛ ቦታ መስጠት ስለ ባህል አንፃራዊነት (cultural relativism) ካለማወቅ የሚመነጭ ግብዝነት ነው። የተበዳይነት ትርክት ከቆየ ታሪክ መዞ አውጥቶ ዛሬ ለማወራረድ መከጀል ዘመኑን የማይመጥን አፍራሽ ዕሳቤ ነው። ሰዎችን ለማፈናቀል የብሔር ካርድ መጠቀምና የሌሎችን መብት ለመጋፋት የአንድነት ካርድ ማውጣት እንደ አገር አለመተማመንን ያስከተሉ አክሳሪ የቁማር ስልቶች ናቸው።

### 3.3 አጀንዳን በቀላሉ ህዝባዊ ማድረግ

የመዋቅር ጥያቄ ሲነሳ በፍጥነት የሕዝብ አጀንዳ ሆኖ ህዝቡ ድጋፉን በውይይት፣ በሰላማዊ ሰልፍና በአመፅ ጭምር ሲሰጥ ይስተዋላል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሃሳቡን ወደ ህዝብ ለማስተላለፍ ቢያንስ ሁለት ምቹ ሁኔታዎች ስለተፈጠሩ ነው። አንደኛው ምቹ ሁኔታ የፖለቲካ አየሩ በተበዳይነት ትርክት መታፈኑሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማህበራዊ ሚድያ ሃይል ነው። በአገራችን የፖለቲካ አየሩ በተበዳይነት ትርክት የተሞላ ነው ማለት ይቻላል። ሁሉም ተበዳይ እስኪመስል ድረስ 'ተገፋሁ' የሚል ድምጽ ከሁሉም ብሔረሰቦች ይሰማል፤ ከሁሉም ቤተ-እምነቶች ይሰማል። ልጆች ከቤተሰብ ጋር አብረው በሚያሳልፉት ጊዜ የሚሰሙት በብሔራቸው ወይም በሃይማኖታቸው ላይ ስለሚደርስ በደል ነው። የተበዳይነት ትርክት ሰዎች በሚሰባሰቡባቸው የትምህርትና የሃይማኖት ተቋማት አካባቢ ሳይቀር የመነጋገሪያ አጀንዳ ናቸው። ስለዚህ የመዋቅር አደረጃጀት የፖለቲካ በደል ማካካሻ መፍትሔ ሆኖ ሲቀርብ አጀንዳው በህዝብ ዘንድ በቀላሉ ተቀባይነት ያገኛል።

ማህበራዊ ሚድያው መረጃን በቀላል ተደራሽ ለማድረግና ወጣቱን ለማሳተፍ ይጠቅማል። ዛሬ የዲጂታል ሚድያ ስብዕና የሚቀረፅበትና ወጣቱ የሚቀሰቀስበት መሳሪያ ሆኗል። ወጣቶች ለማህበራዊ ሚድያ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በጣም የቀረቡ ስለሆነ እነሱን የህዝብ ድምፅ አድርጎ መታገልና በነሱ አማካኝነት መረጃ በቀላሉ ወደ ህዝብ ማድረስ እየተለመደ መጥቷል። ይህ ማለት ሁሉም ተሳታፊ ወጣት ሳይገባው የሌላ ወገን አጀንዳ ያስፈጽማል ማለት አይደለም። ወጣቶች ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና ከፖለቲካ ተሳትፎ በአብዛኛው በመገለላቸው ብሶት አለባቸው። ስለዚህ አንዳንዶቹ ትግሉ ከተሳካ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገብቷቸው በዓላማ ትግል የጀመሩ ይኖራሉ። የዚያኑ ያህል በጥቅም ተታለው፣ በጓደኛ ጫናና በቅስቀሳ ሃይል ተገፋፍተው የተቀላቀሉም ሊኖሩ ይችላሉ።

## 4. የመዋቅር ጥያቄ መዘዞች

### 4.1 የማይመለከታቸው ተጎጂዎች

ኢትዮጵያ ውስጥ ከመዋቅር ጥያቄ ጋር በተገናኘ የሚከሰቱ ግጭቶች በየቦታው ብዙ ዋጋ እያስከፈሉ ይገኛሉ:: የመዋቅር ጠያቂው ህዝብ፣ ምላሽ ሰጪው መንግስት ሆኖ ሳለ ምንም የማይመለከታቸው ንጹሃን ሲሞቱ፣ ሲፈናቀሉ፣ ንብረታቸው ሲወድምና በእስር ሲንገላቱ ይስተዋላል:: በዚህም ሳያበቃ የሚዋደዱ ጎረቤታሞችና አብሮአደግ ጓደኞች በመዋቅር ጥያቄ ምክንያት በክፉ ሲፈላለጉ ማየት ያሳዝናል:: የእልህ ፖለቲካ፣ ብልጣብልጥነት፣ የተበዳይነት ትርክትና እብሪተኝነት በግለሰቦችና በቡድኖች መሃል መተማመን እንዳይኖር አድርጓል:: በማህበራዊ ሚዲያ አንዳንድ ሰዎች ያለመረጃና ያለዕውቀት ሌሎች ደግሞ ሆን ብለው በክፋት ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት የሚለቁትን ውሸትና አሉባልታ ሳያጣሩ የሚሰሙ ጆሮዎች በመኖራቸው የርስ በርስ ጥላቻ እየተስፋፋ ይገኛል:: የሚድያ ዋናው ተልዕኮ እውነተኛና ሚዛናዊ መረጃ ማቅረብና ህብረተሰቡን ማሳወቅ ቢሆንም ዛሬ መረጃ ማሰራጨት የገቢ ምንጭ ስለሆነና መንግስትም ስለማይቆጣጠራቸው ማህበራዊ ሚድያዎች ወደፊትም የግጭት መንስኤና የደህንነት ስጋት ሆነው መቀጠላቸው አይቀርም::

ሴረኞች ማህበራዊ ሚድያን በመጠቀም ግጭት ለመቀስቀስ ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ በተቀነባበረ አካሄድ ታዋቂ ግለሰቦችን ከአንዱ ቡድን ጋር መፈረጅ፣ ስማቸውን በውሸት በማጠልሸት ለጥላቻ ተጋላጭ ማድረግና በቡድኖች መሃል ቅራኔ ማካረር ነው:: ከዚህ አንፃር እኔ ራሴ የገጠመኝን በአብነት ማንሳት እፈልጋለሁ:: ሚያዚያ 01 ቀን 2014 ዓ.ም. በደቡብ ኦሞ ዞን ዋና ከተማ ጂንካና አካባቢዋ በተነሳ ግጭት ክቡር የሰው ህይወት እንደጠፋ፣ የአካል ጉዳት እንደደረሰና ከፍተኛ የቤትና የንብረት ውድመት እንደደረሰ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ማቅረቡ ይታወሳል:: ይህ እጅግ አሳዛኝ፣ አስከፊና የሚወገዝ ግጭት የተቀሰቀሰው ከአሪ ህዝብ የዞን መዋቅር ጥያቄና ምላሽ ጋር የተገናኘ እንደሆነ ተገልጿል:: ግጭቱ በተቀሰቀሰ ዕለት የማይታወቁ ሰዎች በተቀነባበረ የፌስቡክ ዘመቻ በግጭቱ የኔ እጅ ያለበት አስመስለው ፎቶዬን ለጥፈው አሰራጩ:: ይህንን ያደረጉት በአሪ ብሔረሰብና አሪ ባልሆኑ ነዋሪዎች መሃል ጥላቻ፣ ያለመተማመንና የከፋ ግጭት እንዲከሰት የተመኙ መሰሪ ሰዎች ናቸው::

ከድህነት ተነስቼ በትምህርት ከፍተኛ የሚባለው ደረጃ ላይ መድረሴ፣ በአካባቢው የልማት ስራዎችን በመደገፍ በህዝብ ዘንድ ታዋቂነት ማትረፌ፣ ድሽታጊና የሚባለውን የአሪ ህዝብ ጠቃሚ ባህላዊ ዕሴት በኢትዮጵያና በዓለም ላይ እንዲታወቅ አስተዋጽኦ ማድረጌና፣ ወጣቶች በትምህርት ስኬትና በልማት ተሳትፎ እኔን አርአያ ማድረጋቸው ያልተመቻቸው ሰዎች ያሉ ይመስለኛል:: እኔ ከአሪ ብሔረሰብ ተወልጄ በአሪና አሪ ባልሆኑ ሰዎች ድጋፍ በመማር ለከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የበቃሁ ስለሆነ ውለታ ለመክፈል በማሰብ የውጭ አገር ለጋሾችን

በማፈላለግ ያለ ልዩነት ሁሉንም ተጠቃሚ ያደረገ የተማሪዎች መኖሪያ፣ ቤተ-መፃህፍት፣ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣባያ፣ መንገድ፣ ድልድይ እና ሙዚዬም ማሰራት በመቻሌ ዕድለኛ ነኝ። በስብሰባ፣ በሚድያና በጽሑፍ ስለሰላም፣ ትብብርና ልማት ቁርኝት፣ ስለብሔረሰቦች ትስስርና ስለአገር አንድነት ያለኝን ዕውቀት በማጋራትም ዕድለኛ ነበርኩ። ሃላፊነት የጎደላቸው ሰዎች በማይመለከተኝ ጉዳይ በውሸት ስሜን ክፉኛ ያጠለሹ ቢሆንም እኔን የሚገልጹ ከላይ የተዘረዘሩ መልካም ስራዎችን ወደፊትም አጠናክሬ እቀጥላለሁ።

ማህበራዊ ሚድያን ህዝብ ለማጋጨት የሚጠቀሙ ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ የሚሰራው ህጋዊ ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሚድያ አጠቃቀም ዙሪያ ህዝቡ መረጃ ሳያጣራ እንዳያምን የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን መስራት በጣም ያስፈልጋል። የልጆችና ወጣቶች ስብዕና የሚገነባው በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በትምህርት ተቋማት፣ በሚድያና በሃይማኖት ተቋማት ስለሆነ እነዚህ አካላት በዚህ የማንቃት ሥራ ላይ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ አለባቸው። የመልካም ስብዕና መገለጫዎች ርህራሄ፣ ሐቀኝነት፣ ቀናነት፣ ተስፈኝነት፣ በራስ መተማመን፣ የራስን ጥንካሬና ድክመት ማወቅ፣ ስኬታማነት፣ ደስተኛ መሆን፣ ይሉኝታ፣ ለሌላ ሰው ማሰብ፣ ፈሪሃ-እግዚአብሄር ናቸው። ነገር ግን የመዋቅር ጥያቄም ይሁን ሌላ አነጋጋሪ የፖለቲካና የሃይማኖት ጉዳዮች ሲነሱ የሚሰተዋለው የጥላቻ ንግግር፣ የሐሰት ውንጀላ፣ የጭካኔ ተግባራት፣ በግፍ ሰው መጉዳትና የመሳሰሉ ክስተቶች በእርግጠኝነት የስብዕና ግንባታ ችግር መኖሩን ያሳያሉ።

## 4.2 የድህረ-መከፋፈል ስጋቶች

የቀድሞ ደቡብ ክልል መስተዳድር በምሁራን ያስጠናው ጥናት የመዋቅር ጥያቄ በርካታ ስጋቶች ያዘለ መሆኑን አሳይቷል። ጥያቄዎች ሕገ-መንግስታዊ ቢሆኑም ለጠየቀ ሁሉ ሊፈቀድ ስለማይችል ለአንዱ ፈቅዶ ለሌላው መከልከል በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ያሳጣል። ብሔር-ተኮር ክልሎች ከበዙ የከረረ ብሔርተኝነት ዕሳቤ አይሎ የአገር አንድነትን ለማስጠበቅ ያስቸግራል። የአዳዲስ ክልሎች መፈጠር በጋራ ሃብት አጠቃቀምና በመሬት ይገባኛል ጥያቄ ወደ ማያባራ ግጭት ሊያስገባ ይችላል። መዋቅር ሲሰፋ የአስተዳደር ወጭ ስለሚጨምር ለልማት ሊውል የሚችል ሀብት መባከኑ አይቀርም። ከፌደራል መንግስት የሚላከው የድጎማ ገንዘብ የተወሰነ ስለሆነ አዲስ ክልል ሲጨመር የሌሎች ክልሎች ድርሻ ስለሚቀንስ በክልሎች መካከል መስማማት ካልተቻለ አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል። ትናንሽ ክልሎች እንደትላልቆቹ ክልሎች በአገር ደረጃ የተደማጭነትና ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም አይኖራቸውም።

ከዚህ የምንረዳው የመዋቅር ጥያቄ በጥንቃቄ እየታየ ምላሽ ካልተሰጠ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑን ነው። ስለዚህ ጥያቄ አቅራቢው ቡድንም ሆነ ምላሽ ሰጪው የመንግስት አካል መልካም ዕድሎችንና ስጋቶችን ማመዛዘን አለበት። የሚገባቸው እንዳይከለከሉና ከህዝብና

ከአገር ፍላጎት አንፃር ግልጽ ስጋት እያለ የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይወሰን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው መፍትሔ መተማመንን በማስፈን ለመዋቅር ጥያቄ ምክንያት የሚሆነውን የአለመተማመን መንስዔዎችን ማስወገድ ነው። በአዲስ የአስተዳደር መዋቅር ለማሳካት የሚፈልጉትን ዓላማ በነባሩ መዋቅር የሚሳካ ከሆነ የአደረጃጀት ጥያቄ ህዝባዊ አጀንዳ የሚሆንበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው። ነባሩ መዋቅር በህዝቦች ማህበራዊ መሰረት ውስብስብነትም ሆነ በራሱ የአደረጃጀት ቁመና የመልማት ጥያቄዎችን መመለስ የማይችል ከሆነ የመዋቅር ጥያቄውን መፍቀድ የግድ ይላል።

የአስተዳደር መዋቅሮች ብሔር-ተኮር መሆን አላባቸው ወይስ መልክዓምድራዊ የሚለው ጥያቄ አነጋጋሪና አካራካሪ ሆኖ ቀጥሏል። አከራካሪ የሆነበት ዋናው ምክንያት ሁለቱም አማራጮች በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ተቀባይነት ስላላቸው ነው። በዚህ ጉዳይ በህዝብ ውስጥ የተያዘው ዓቋም ጠንካራ ስለሆነ አንዱን አማራጭ መሬት ላይ ለመተግበር የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን ማስቀየምና ሌላውን ማስደሰት ይሆናል። የፖለቲካ ስርዓቱ አለመተማመን የነገሰበት ከሆነ መዋቅሩ በብሔርም ይደራጅ በመሬት አቀመመጥ ብዙ የሚያመጣው ለውጥ የለም። መተማመንን ማስፈን ከተቻለ በማንነት ማሰብና በብሔር መጠለል ስለሚቀንስ የመዋቅር መስፈርት የአስተዳደር አመችነት ብቻ ይሆናል።

## 5. ማጠቃለያ

መተማመን በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ጤናማ ግንኙነት ለመገንባት፣ ሰላም ለማስፈን፣ ልማትን ለማሳለጥ፣ ብልፅግና ለማምጣትና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋግጥ ይረዳል። በተለያየ ምክንያት  መተማመን ጠፍቶ አለመተማመን ሲሰፍን እነዚህ መልካም ውጤቶች በተገላቢጦሽ ይገለጻሉ፤ ግንኙነት ይቋረጣል፣ ሰላም ይጠፋል፣ ልማት ይስተጓጎላል፣ ብልጽግና አይመጣም፣ የጋራ ተጠቃሚነትም አይረጋገጥም። በነባሩ ግንኙነትና ስርዓት መቀጠል የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመቋቋም ከባድ በሚሆንበት ጊዜ እንደ ህልውና ጥያቄ ይታሰብና ሰዎች ሌላ አዲስ አማራጭ ለማፈላለግ ይገደዳሉ። በአማራጭ ፍልጋ ሂደቱ ወቅት ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ የህግ አግባቦችን፣ መልካም ዕድሎችንና ማስፈጸሚያ ስልቶችን ይጠቀማሉ። ኢትዮጵያን በተለይም የቀድሞ ደቡብ ክልልን በአንድ ወቅት ያጥለቀለቀው የመዋቅር ጥያቄ በዚህ ንድፈ-ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል።

የቀድሞ የደቡብ ክልል 56 ብሔረሰቦችን አካቶ በአንድ የክልል አደረጃጀት ሲዋቀር ሁሉም ብሔረሰቦች በእኩልነትና በፍትሐዊነት ይተደደራሉ፣ ሰላም ይሰፍናል፣ ልማት ይፋጠናል እንዲሁም የጋራ ተጠቃሚነት ይረጋገጣል የሚል እምነት ነበር። ነገር ግን የክልሉ ስልጣን በጥቂት ቡድኖች እጅ በመውደቁ የተነሳ የጋራ ተጠቃሚነትን ማራጋገጥ ባለመቻሉ አለመተማመን መፈጠሩን ክልሉ ራሱ ያስጠናው ሳይንሳዊ ጥናት ያረጋግጣል። ክልሉ እምነት ካጣባቸው ምክንያቶች ወስጥ በበጀት አጠቃቀም ግልጸነት  አለመኖር፣ የትላልቅ ፕሮጀክቶች

ስርጭት ያለመመጣጠን፣ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታ ፍትሐዊ አለመሆን፣ የሐዋሳ ከተማ ሲቀር ሌሎች ከተሞች አለማደጋቸው፣ በፍትህ ስርዓቱ አድሏዊ አሰራር መስፈን፣ የህግ የበላይነት አለመከበር፣ የደህንነት ስጋት መጋረጥና ሹመትና ምደባ በወገንተኝነትና በጥቅም መሆን የሚሉት ይገኙበታል።

በዚህ የተነሳ ዞኖች ወደ ክልል ለማደግ ሲጠይቁ አመቺ ሁኔታዎችን ለይተው በመጠቀም ነበር። እነዚህም ሕገ-መንግስዊነትን መነሻ ማድረግ፣ የመልማት ጥያቄ አግባብነትን ማስረገጥ፣ የማንነት ካርድና የተበዳይ ትርክትን መጠቀም፣ ወጣቶችን የትግሉ አንቀሳቃሽና አቀጣጣይ ኃይል ማድረግ፣ ማህበራዊ ሚድያን በስፋት መጠቀም፣ አጀንዳውን ህዝባዊ ማድረግ እና የፌደራል መንግስት በጫና ጥያቄውን ማስቆም የማይችልበትን ጊዜ መምረጥ ናቸው። እምነት የታጣበት የቀድሞ ደቡብ ክልል አራት አዲስ ክልሎችን አዋቅሮ መፍረሱ የግድ ሆኗል። ክልል የመሆን ጥያቄ ያቀረቡት ዞኖች በሙሉ ክልል ባይሆኑም አለመተማመን የፈጠረው የመበተን አደጋ በዚህ መልክ ተቋጭቷል።

የመተማመን-አለመተማመን ንድፈ-ሃሳብ ያለፈውን ክስተት ለመረዳት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊከሰት የሚችል የመበታተን ስጋትን ከወዲሁ በመለየት መፍትሔ ለመፈለግ ይረዳል። አዲሶቹ ህብረ-ብሔራዊ ክልሎችም ሆኑ ሌሎች መሰል የአስተዳደር መዋቅሮች ከቀድሞ የደቡብ ክልል ስህተት በመማር መተማመንን ማስፈን ካልቻሉ አለመተማመን ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ የአለመተማመን ችግር የሚስተዋለው ከመዋቅር ጥያቄ ጋር በተገናኘ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የግንኙነት መስመሮች እየሰፋ በመምጣት በህዝብና በመንግስት መሃል ክፍተት እየፈጠረ ስለሆነ በልዩ ትኩረት መተማመን ሊገነባ ይገባል።

መተማመንን ለማስፈን በግለሰብና በተቋማት ደረጃ መወገድ ያለባቸው ጎጂ ልምዶችና መዳበር ያለባቸው ጠቃሚ ዕሴቶች አሉ። መወገዝና መወገድ ያላባቸው ጎጂ ባህሪያት ውሸት፣ ስርቆት፣ ክህደት፣ ብልጣብልጠት፣ አስመሳይነት፣ አጭበርባሪነት፣ አድሏዊነት፣ ኢ-ፍትሐዊነት፣ ጥቅመኝነት፣ ገፊነትና ግፈኝነት ይገኙባቸዋል። በነዚህ አሉታዊ ባህሪያት ምክንያት የሚከሰተውን አለመተማመን ለማስወገድ መዳበርና መተግበር ያለባቸው ጠቃሚ ዕሴቶች ደግሞ እውነተኝነት፣ ታማኝነት፣ ችሎታ፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ አካታችነት፣ ምላሽ ሰጭነት፣ እና የህግ የበላይነት ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ እውነት መናገር፣ ታማኝነት፣ አቃፊነት፣ ተካፍሎ መብላት፣ ሃላፊነት መውሰድ፣ የሰውን አለመመኘት፣ ሌብነትን መጸየፍና ስግብግብነትን ማውገዝ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶች ስለሆኑ እንዲጠናከሩ ማድረግ ይቻላል። እንደ ህዝብ ዛሬም ኢትዮጵያዊያን ህግ አክባሪና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ናቸው። ስለዚህ መተማመንን ለማስፈን ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው። ነገር ግን እነዚህን እሴቶች በወቅቱ ካልተጠቀምንባቸው እድሉ እየጠበበ መሄዱ ስለማይቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከተን ሁሉ (ከተራ ዜጋ እስከ ከፍተኛው የመንግስት አካል) መፍጠን ይኖርብናል።

**Reference**

Arrow Kenneth. 1974. The Limits of Organization. New York: Norton

Banfield, EDWARD. 1958. The Moral Basis of a Backward Society. Glencoe, IL: Free Press.

Coleman, James. 1988. Social Capital in the Creation of Human Capital. American Journal of Sociology, 94: 95-120.

Coleman, James. 1990. Foundations of Social Theory. Cambridge, MA and London: Belknap Press of Harvard University Press.

Fukuyama, Francis. 1995. Trust: The Social Virtues and the Creation of Prosperity. New York: Free Press

Parsons, Talcot. 1937. The structure of social action. New York: McGrawHill.

Paxton, Pamela. 2002. Social Capital and Democracy: An Interdependent Relationship. American Sociological Review, Vol. 67(2): 254-277.

Simmel, George. 1906. The Sociology of Secrecy and of Secret Societies. American Journal of Sociology, 11 (4):441-498.

# IV. ለዲሞክራሲያዊ ፌዴራል ሥርዓት መገንባት አንዳንድ አስተያየት

አንዳርጋቸው አሰግድ

- የማጋራው፣ የአንድ—ከወጣትነት ዘመኑ ጀመሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የኖረን እና እስካሁንም ድረስ የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሚከታተልን ግለሰብ አስተያየት ነው:: አንዳንዴም፣ እዚህ እና እዚያ የታዘብኩትን::
- በርዕሱ ለማመልከት የፈለኩት፤ የኢትዮጵያ "ፌደራል" ሥርዓት ዲሞክራሲያዊም ፌደራልም እንዳልሆነ ነው:: ወይንም፤ ዲሞክራሲያዊ ፌደራል ሥርዓት ገና መገንባት ያለበት ሥርዓት መሆኑን ነው::
- በመጀመሪያ፣ ስለኖርንባቸው የአገዛዝ ሥርዓቶች በጥቂቱ አነሳለሁ:: በተለይም በድኅረ-1983ቱ ላይ አተኩሬ አንዳንድ አመለካከቴን አጋራለሁ::
- በመጨረሻም፣ በቃላት እና በፅንሰ—ሃሳቦች አረዳድ እና አጠቃቀም ረገድ የሚታዩኝን እንዳንድ ጉዳዮች  አስታውሼ አጠቃልላለሁ::
- "መንግሥት" የሚለውን ቃል የምጠቀመው፤ "state" ለሚለው ነው:: "መስተዳድር" የሚለውን የምጠቀመው ደግሞ "government" ለሚለው ነው::

## መግቢያ

የኖርንባቸው የአገዛዝ ዓይነቶች፣ የመሣፍንታዊ/ንጉሣዊ፣ የወታደራዊ እና የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ዓይነቶች ይባሉ እንጂ፤ ሁሉም የአንድ—የፍፁማዊ ሥልጣን ባለቤት የሆነ ግለሰብ አገዛዝ ዓይነቶች ነበሩ:: የአገዛዝ ሥርዓቶቹ፣ "ንጉሠ—ነገሥታዊ"፣ "ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ" እና "ፌደራላዊ ዲሞክራሲ" በመባል ይሰየሙ እንጂ፤ ሁሉም የአሓዳዊ አገዛዝ ሥርዓቶች ነበሩ:: በሁሉም ሥርዓቶች፤ ገዢ እና መንግሥት፣ ገዢ እና መስተዳድር ተለያየተው አያውቁም:: "የሥራ አስፈፃሚ"፣ "የምክር ቤት"፣ "የፍትሕ"  የሚባሉት የመስተዳድር አካላት ነፃ ህልውና ኖሯቸው አያውቅም::

በሶስቱም የአገዛዝ ሥርዓቶች በርካት ዕውቅና የሚገባቸው የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የፋይናንስ፣ የመንገድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን...ወዘተ. ዕድገቶች ተከናውነዋል:: በሌላው በኩል ብሔራዊ ሀብቶች ለውጭ ባለሀብቶች ሽያጭ እየቀረቡ ነው:: የባንክ መስክ

ለውጭ ባለሀብቶች እንደሚከፈት ተገልጿል። ምንም ዓይነት የረባ አገራዊ ውይይት እና ምክክር ሳይደረግባቸው ወደ እርምጃ መገባቱ በእጅግ ያሳስባል። በቀጥታ የሚመለከታቸው ክፍሎች እንኳን ተሳታፊ አለመደረጋቸው፤ ይብሱን አሳሳቢ ያደርገዋል። ሌላም፤ ተፈጥሯቸው በዘር ምህንድስና የተለወጠ ዘር—አልባ የጥጥ ዘሮች በሰፋፊ እርሻዎች እየተዘሩ ይገኛሉ። በቆሎ እና እንስት ተራቸውን እየጠበቁ እንደሆነም ተነግሯል። እነዚህ እና እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ከአገራዊ መግባባት ላይ እስከሚደረስ ድረስ ሂደቱን ማገድ የተሻለው መንገድ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። የዘሮች ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ፣ እንደ ሞንሳንቶ እና ባየር ያሉትን የዘር—አልባ ዘር አምራች ኩባንያዎች ኪስ ለማደለብ መቅረብ የለባትም። እንደዚሁም፤ በመስተዳድር እና በዕምነት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ልዩነት ጥያቄዎች እየተነሱ ነው። አንዳንድ ጥናታዊ ጽሑፎችም እየወጡ ነው። ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ የማኀበራዊ—ፖለቲካ ጥናት ተመራማሪዎች ሊመለከቱት የሚገባ ጉዳይ ነው ብዬ አምናለሁ።

ወደ ውይይቱ ርዕስ ለመመለስ፤ ቀደም ያሉት ዓመታት በፓርቲዎች መፈልፈል ረገድ ዓይነተኛ ነበሩ ማለት ይቻላል። የቅርብ ጊዜ ዓመታት፣ በክልሎች መበራከት ዓይነተኛ እየሆኑ መጥተዋል።  እንደኔ እምነት በዚህ አኳያ ሊጠየቁ የሚገባቸው የመጀመሪያዎቹ ጥያቄዎች፤ በኢትዮጵያ ምድር ከ20ኛው ዓመታት ጀምሮ ለሪፎርም እና ለመሠረታዊ ለውጥ የታገሉት አገር—አቀፍ ምሁራን እና የአብዮት ኃይሎች ለምን ተዳከሙ? ወይንም፤ የብሔር ድርጅቶች ለምን በኢትዮጵያ ምድር ደረጁ? እንደምንስ ፈርጥመው ለሥልጣን ባለቤትነት በቁ? የሕወሓት አመራር በምን ዓይነት የአገዛዝ ዘይቤ እና ሥርዓት ለዓመታት ዘለቀ? የሕወሓት አመራር የአገዛዝ ዘይቤ እና ሥርዓት ከተበተበው ሰንኮፍ እንደምን ይወጣ? የሚሉት ጥያቄዎች ይመስሉኛል።

## ስለ ብሔር ድርጅቶች መስፋፋት

የጥያቄዎቹ መልሶች ለዚህ መድረክ ተሳታፊዎች የማይታወቁ እንደማይሆኑ እገምታለሁ። ለማስታወስ ያህል፣ በኢትዮጵያ ምድር ለብሔር ድርጅቶች መናኘት ዋናውን አስተዋፅኦ ያደረገው አገራዊ ሁኔታ፣ ኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊነት ለመሻገር ብታቀናም፤ በአንፃሩ መካሄድ እና መፈፀም የነበረባቸው አስፈላጊ ሪፎርሞች ሳይደረጉ በመቅረታቸው ምክንያት እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። አስፈላጊ የነበሩት ሪፎርሞች አለመካሄዳቸው፣ ሁለት የተያያዙ የፖለቲካ ሁኔታዎችን እንዳስከተሉም፤ እንደዚሁ ተደጋግሞ ተገልጿል። በአንድ በኩልአገራዊ ተቀባይነት እና ቅቡልነት ያላቸው የሪፎርም ኃይሎች ለመውጣት እና አገራዊ ተፅእኖ ለማሳረፍ ሳይችሉ ቀሩ። በሌላው በኩል፣ በተለይም በተማሪው እና በምሁራኑ ለሥርዓታዊ ለውጥ የተደረገው ትግል፣ ይህ ነው የሚባል የሰላማዊ ትግል ዘመን ዕድሜ ሳይቆጥር፣ ወደ መሣሪያ ትግል ተገባ። እነዚህ የተያያዙ ጉዳዮች ይመስሉኛል፤ በአንድ ወገን፣ የ1966 አብዮትን እጅግ ሥር—

ነቀል ያደረጉት:: በሌላውም ወገን፣ የአብዮቱን ተዋናይ ኃይሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ግጭት የወሰዱት:: ባጭሩ ብንመለስባቸው፦

ኢትዮጵያ—ቢያንስ በራስ ተፈሪ እና በአፄ ኃይለሥላሤ ዘመን፣ የሪፎርም አቀንቃኝ ምሁራን ነበሯት:: ከ*አእምሮ፣ ብርሃን እና ሰላም* እና ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ "Pioneers of Change" እስካሏቸው ድረስ የነበሩት አገር—ወዳድ ምሁራን እና ልሂቃን ለሪፎርም የተነሳሱ እና ያሳሰቡ ነበሩ:: ከፋሺስት ወረራ በኋላ በነበረው ዘመንም፣ ኤርትራ የነፃ ጋዜጦች ባለቤት ለመሆን በቅታ ነበር:: የ1953 የንዋይ ወንድማማቾች የመፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ የማንቂያ ደወል ነበር:: ከዝያም፤ አቶ ሃዲስ አለማየሁ፣ ደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት፣ ጄነራል አቢይ አበበ፣ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት፣ ጄነራል ከበደ ገብሬን የመሳሰሉ እና ሌሎች የንጉሠ—ነገሥቱ ባለሥልጣኖች፤ የሪፎርም እርምጃዎች እንዲወሰዱ ብዙ አሳስበው ነበር:: ከደራሲያንም፤ እነ ፀጋዬ ገብረ መድሕን "ዋ! ያች አድዋ!" እያሉ ጮኸው ነበር:: እነ አቤ ጉበኛ "አልወለደም" እያሉ እና "ዕድል ወይንስ በደል" እያሉ ጠይቀው ነበር::

ይሁን እንጂ፤ እኛ በ60ው ዘመን የኢትዮጵያ 'ጃፓናይዘርስ' እንላቸው የነበሩት ምሁራን፣ የንጉሠ—ነገሥቱ ዘመን ሊብራል ባለሥልጣኖች እና ደራሲያን ያቀረቧቸው የሪፎርም ጥሪዎች፤ ራስ ተፈሪ ከአልጋ ወራሽነት ወደ አፄነት ባደረጉት ጉዞ አድማጭ እያጡ ሄደው መከኑ:: የኤርትራ ነፃ ጋዜጦች፣ የፌደሬሽኑ ውል ሲፈርስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ መሥመር ገቡ:: ሊብራል ባለ ሥልጣኖቹም አድማጭ እንዳጡ፣ የየካቲት 1966 አብዮት ፈነዳ:: ወይንም፤ የሪፎርም አቀንቃኞቹ ጥሪዎች ወደ ሕዝባዊ ማኅበራዊ—ፖለቲካ እንቅስቃሴ ሳያድጉ፤ የ1966 አብዮት ተቀጣጠለ::

የአገር—ወዳድ ተማሪዎች እና ምሁራን የሪፎርም ጥሪ እንቅስቃሴ በ50ው ዓመታት አጋማሽ ላይ ጀመረ:: ይሁንና፣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ሥር—ነቀል ንቅናቄ ተሻገረ:: ብዙም ሳይቆይ፤ ወደ ትጥቅ ትግል አቀና:: መለስ ብለን ብናስታውስ፣ "የመሬት ለአራሹ" ጥሪ በ1957 ቀረበ:: "ድህነት ወንጀል ነው ወይ?" እና "ሥራ ለሥራ አጦች" የሚሉ ሰልፎች በ1959 ተካሄዱ:: ጥላሁን ግዛው በ1962 ተገደለ:: የእሱ መገደል እና በማግሥቱ የደረሰው የ20 ተማሪዎች ሕይወት ማለፍ አንዳንዶቹን ፦

> "በታህሣሥ 1962 የፊውዶ—ፋሺዝምን እና የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ለመጠበቅ ያገሩት ጠብመንጃዎች፣ ላንሰራራው የኢትዮጵያ አብዮት አመፅ ጥምቀቱ እንደነበሩ መታወቅ አለበት፤ የኢትዮጵያን አብዮት ከእንግዲህ ወዲህ መሣሪያን ባላነሳ የተማሪ እንቅስቃሴ ክልል ውስጥ ልናስበው አንችልም" ወደሚለው የትግል ስልት ወሰደ (Spark News Letter 1963):: በዛም አነሰ አመርቂ የሰላማዊው ፖለቲካ ትግል ዘመን ሳይኖር በፊት፣ የሪፎርም ጥሪው እና ንቅናቄ፣ በዛም አነስ የተወሰነ ማኅበራዊ—ፖለቲካ መሠረት ሳይዝ በፊት፣ የሰላማዊ ትግል በሮች ተጠርቅመው ሳይዘጉ በፊት፣

1962 በዚሁ፣ የኢትዮጵያ ተማሪ እና ምሁራን በተለይም በትግል ስልት ጥያቄ በተነሱ ልዩነቶች ምክንያት፤ የተከፋፈሉበት ዓመት ሆነ። ከፊሉ በንቃት/ድርጅት መስመር ተሰለፈ። ከፊሉ የፖለቲካ ትግሉን በትጥቅ ትግል ቀድሶ በትጥቅ ትግል ወደ መጨረስ አመራ። ከፊሉም የየብሔሩን የትጥቅ ትግል ወደመጀመር አቀና። ዘመኑ የራሱ ሚና ነበረው።

ዘመኑ ከቪዬትናም እስከ ኩባ፣ ከአልጄሪያ እስከ ደቡብ አፍሪካ የትጥቅ ትግሎች የሚካሄዱበት ዘመን ነበር። የቼ ጉቬራ እና የሬጂስ ደብሬ "ጥቂት የታጠቁ ይበቃሉ" የሚለው የትግል ስልት የገነነበት ዘመን ነበር። የፓለስታይን ታጋዮች አውሮፕላን እየጠለፉ ጭምር ትግላቸውን የሚያስተዋውቁበት ዘመን ነበር። በአሜሪካ *ብላክ ፓንተርስ* እና *ቱፓማሮስ* የሚባሉት እና በአውሮፓ *ባደር ማይንሆፍ* እና *ሬድ ብሪጌድ* የሚባሉት፣ በከተማ ትጥቅ ትግል የተሰማሩበት ዘመን ነበር። "የፖለቲካ ሥልጣን የሚመነጨው ከጠብመንጃ አፈሙዝ ነው" የሚለው የማኦ ትሴ ቱንግ ቀኖናም የገነነበት ዘመን ነበር።

ነገሮች በእንዲህ  እንዳሉ እና የየትኛውንም የኢትዮጵያ አብዮተኛ የትግል ስልት ከሂሳቡ ሳያስገባ፤ የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት ፈነዳ። ወታደራዊው ገዢ ቡድን ወይንም ደርግ የሥልጣን ባለቤት ሆነ። ደርግ በጫጉላ ዘመኑ ከ"ኢትዮጵያ ትቅደም" እስከ "የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት"፣ "ከኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት" እስከ "መሬት ለአራሹ" አዋጅ እና እስከ "ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም" መውጣት ድረስ የሪፎርም እና የመሠረታዊ ለውጥ እርምጃዎችን ወሰደ። ከፊሉ አብዮት በመካሄድ ላይ መሆኑን ተቀብሎ፤ በንቃት/ድርጅት መስመሩ ቀጠለ።  ወደ መሣሪያ ትግል አቅንቶ የነበረው ከፊል፣ "አብዮት አልተካሄደም" እያለ እና "ፋሺስት" ያለውን ሥርዓት እያወገዘ፤ በመሣሪያ ትግሉ ገፋ።

ይህ ሲታወስ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለታሪክ ገፆች የሚበቃ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግል ዘመን ነበር ለማለት አይቻልም። በዚህ ረገድ የነበረው ጉድለትም ይመስለኛል ከ1969 የከተማ የትጥቅ ትግል አንስቶ እስከ 1970 የሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም አብዮታዊ ሰደድ እና በኋላም እስከ ኢሠፓ መንግሥታዊ ሽብር ዘመን ድረስ የወሰደው። በሂደቱ ውስጥ፣ በ60ዎቹ ዘመን በአገር—አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው ከነበሩት አገር—ወዳድ እና አብዮታዊ ምሁራን እና የሠራዊት ልሂቃን መካከል ብዙዎች በግፍ ተገደሉ። ሌሎቹ የብዙ ዓመታትን የእሥር ዘመን ቆጠሩ። ከፊሉ ለስደት ሕይወት ተዳረገ።

የኢትዮጵያ አገር—ወዳድ እና አብዮታዊ ምሁራን እና የሠራዊት ልሂቃን ለመንግሥታዊ ሽብር ተዳርገው የተደቆሱት ለመጀመሪያ ጊዜ አልነበረም። ግራዚያኒ በ1929 በአዲስ አበባ ከተማ በነዛው የሦስት ቀናት ሽብር ከ300 የማያንሱ ተጨፍጭፈው ነበር። የእነርሱ መቀጠፍ፣ የ20ኛውን ዘመን የለውጥ እንቅስቃሴ የቱን ያህል እንደጎዳ በዕርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም።

ጎሬ ላይ የኢትዮጵያን ሬፓብሊክ እስከማቋቋም የደረሰ እንቅስቃሴ ተጀምሮ እንደነበር ሲታወስ፤ አነስተኛ እንዳልነበር ለመገመት አያዳግትም።

ከ1969 ጀምሮ በተካሄደው የከተማ ትጥቅ ትግል እና የመንግሥት ሽብር፤ የኢትዮጵያ አገር—አቀፍ አገር—ወዳድ እና አብዮታዊ ወጣቶች፣ ምሁራን እና የሠራዊት ልሂቃን ተመናምነው እና ተዳክመው ከጨዋታው ውጭ መደረጋቸው እውነታ ነው። ብዛታቸው እስካሁን በውል አይታወቅም። ተከታዩ ትውልድ—አንዲት ወጣት በቁጭት እንዳለችኝ— በአንድ ወገን "ተንጠልጥሎ ቀረ"። በሌላው ወገን "ፖለቲካ እና ኮረንቲ..." እያለ፣ ወደፐሪሜር ሊጎች መከታተል ዞረ። የብሔር ድርጅቶች እና ኢሠፓ የፖለቲካ ሜዳውን ለ14 ዓመታት ይዘው ናኙ— ተከታዩ ትውልድ ጊዜውን ቆጥሮ እስኪነሳ ድረስ።

ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ ሰደድ፣ ኢሠፓአኮ እና ኢሠፓ እያሉ የራሳቸውን አገር-አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ወደ ማቋቋም አመሩ። ኢሠፓ ተቋቋመ። ከዚያም፣ "ሕዝባዊ ሪፐብሊክ" የተባለ መንግስት በይፋ ተመሠረተ። በሂደቱ፣ በአብዮቱ ጫጉላ ዘመን አብበው የነበሩት ነፃ ሕዝባዊ ድርጅቶች ሕዝባዊነታቸውን ተገፈው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የኢሠፓ አገዛዝ የጭቆና መሣሪያዎች ሆነው አበቁ። በገዢ ፓርቲ እና በመስተዳደሩ መካከል ሊኖር የሚገባው ልዩነት ደብዛው ጠፋ።

በእኔ እይታ — የተመለከቱት ክንዋኔዎች ድምር ነው፤ በአንድ ወገን ለብሔር ድርጅቶች መደርጀት እና መፈርጠም የበጀን ሁኔታ አንጣሎ ያሰፈነው። በሌላውም ወገን እና የኢትዮጵያ አገር—አቀፍ አገር ወዳድ እና አብዮታዊ የፖለቲካ ኃይሎች የተዳከሙትን ያህል፤ የሥልጣን ትንቅንቁን በብሔር ድርጅቶች እና በሥልጣን ባለቤቱ ኢሠፓ መካከል ያደረገው።

የኢሠፓ መስተዳድር ከሶቪየት ኅብረት እና ከሰሜን ኮሪያ ጎራ የገባውን ያህል፤ የብሔር ድርጅቶቹ በፀረ—ሶቪየት መሥመር በተሰለፈው በምዕራቡ ዓለም፣ በአረብ አገሮች፣ በሱዳን እና በሶማሊያ ገዢዎች እርዳታ ጭምር እየታገዙ ፈረጠሙ። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ የ1977 ዓ.ም. ርሃብ ለሕወሓት አመራር መደርጀት እና መፈርጠም የራሱን ሚና ተጫወተ። መንግሥታዊ ያልሆኑ የሚባሉት የምዕራቡ ዓለም ድርጅቶች (NGOs) በኮንሰርቲየም ተቀናጅተው የተጫወቱት አሉታዊ ሚና ለወደፊት በጥልቀት መመርመር እና መጠናት ያለበት ጉዳይ ነው። ደግሞም፣ ዛሬም የሚጫወቱት ሚና አለ። መንግሥታዊ ያልሆኑ የሚባሉት የምዕራቡ ዓለም ድርጅቶች የየመንግሥታቱ የውጭ ፖሊሲ መሣሪያዎች መሆናቸው ይታወቃል።

የኢሠፓ መስተዳደር የኢትዮጵያን ብሔሮች ጥያቄ በአንድ ወገን "አንድ ሰው እና አንድ ጠብመንጃ እስኪቀር ድርስ" ባለው የወታደራዊ መፍትሔ አካሄድ ሊፈታ ሞከረ። በሌላው ወገን፣ ኢሠፓ ካድሬዎቹን በሠራዊቱ ውስጥ ሰግሥጎ፤ የሠራዊቱን የአመራር ሥልጣን እርከን እና የእዝ መሥመር አመሳቀለ። ይህም ብቻ አልነበረም። ወቅቱ አሁን ይልቁኑ ደግሞ፤

በተለይም በሠራዊቱ አገር ወዳድ ልሂቃን መጨፍጭፍ ዓይነተኛ ሆነ። ኢሕአዴግ በሚል ስያሜ የተደራጀው የብሔር ድርጅቶች "ግንባር"፤ የማታ ማታ አሸነፈ።

የኢትዮጵያ አገር ወዳድ እና አብዮታዊ ሲቪሎች እና የሠራዊቱ ልሂቃን ከ1969 እስከ 1983 ለ14 ዓመታት በአብዮታዊ ሰደድ እና በኢሠፓ መስተዳድር መንግሥታዊ ሽብር ተጨፍጭፈው በተመናመኑበት ሁኔታ፤ አገራዊው የፖለቲካ ሜዳ በብሔር ድርጅቶች መያዙ የሚያስገርም አይደለም። የብሔር ድርጅቶቹ በወቅቱ በነበረው ዓለም አቀፋዊ አሰላለፍ በምዕራባዊያን እና በአንዳንድ የአረብ አገሮች ታግዘው ጭምር መደርጀታቸው እና መፈርጠማቸውም የሚያስገርም አይደለም። ውሎ አድሮ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተተፋውን የኢሠፓ መስተዳደር ለመገርሰስ መብቃታቸውም እንደዚሁ አያስገርምም። ይልቁኑ የሚያስገርመው "ለአርነት እና ለነፃነት እንታገላለን" የሚሉት የብሔር ድርጅቶች የመሠረቱት የአገዛዝ ዘይቤ እና የአገዛዝ ሥርዓት ነው።

በምንም መሥፈርት የነፃ ድርጅቶች ስብስብ ሊባል የማይችል ድርጅት፣ "ግንባር" ተብሎ በግንቦት 1983 ዓ.ም. የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሆነ። በምንም መሥፈርት "ድርጅት" ተብለው ሊጠሩ የማይችሉ የብሔር ድርጅቶች ከመቅፅበት ተፈለፈሉ። በምንም መሥፈርት የሽግግር ዘመን ሥርዓት ሊባል በማይችል "ሽግግር" ተሳታፊ ሆኑ። በሌላው በኩል፣ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዲኃቅ) ዙሪያ ተሰባስበው የነበሩት የኢትዮጵያ አገር ወዳድ እና አብዮታዊ ኃይሎች ከተሳትፎ ታገዱ። ፕሮፌሰር አሥራትን የመሳሰሉ አገር—ወዳድ፣ ለእሥራት እና ሕልፈት ተዳረጉ። ኦነግን፣ የሲዳማ ንቅናቄን እና ኦብነግን የመሳሰሉት ነፃ የብሔር ድርጅቶች፤ "እንዳያማህ ጥራው፣ እንዳይበላ ግፋው" በሚል ፖለቲካ፤ ለእይታ አፍታ ያህል እንዲታዩ ተደርገው ተሸኙ። የመንግሥት ሥልጣን ተጠቃሎ፣ ግንባር ያልሆነውን ግንባር በሚመራው እና የፖለቲካ ሂደቱን እና ክንዋኔ በብቸኝነት በሚቆጣጠረው የሕወሓት አመራር ተያዘ። ኢትዮጵያም—ለስንተኛ ጊዜ፣ በአንድ የፍፁማዊ ሥልጣን ባለቤት በሆነ ግለሰብ መዳፍ ውስጥ ወደቀች። ይህም ሁሉ የተካሄደው፣ በምዕራቡ ዓለም—በተለይም በአሜሪካ እና በእንግሊዝ መንግሥታት ዕውቅና እና ያላሰለሰ ድጋፍ እየታገዘ ነበር፤ በግብፅ፣ በሱዳን እና በአንዳንድ አረብ አገሮች እገዛ ነበር።

የሕወሓት አመራር ምን ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት አቀመ? ውጤቱ ምን ሆነ? ወዴት ሊያመራ ይችላል?

## የሕወሓት አመራር የአገዛዝ ዘይቤ እና የአገዛዝ ሥርዓት

የሕወሓት አመራር ግንባር ያልሆነውን ድርጅቱን "ግንባር" እንደሚለው ሁሉ፤ ያቋቋመውን ዲሞክራሲያዊ ያልሆነውም አገዛዝ "ዲሞክራሲያዊ" እያለ እና "ኢትዮጵያ ወደ ብዝኃ-ፓርቲ ሥርዓት ተሻግራለች" እያለ አስተዋወቀ። ኢትዮጵያን በአንድ የሕወሓት አመራር "አብዮታዊ

ዲሞክራሲ” ፓርቲ አደረጃጀት አማክሎ ለ27 ዓመት ገዛ። በስመ “ፌዴራል ሥርዓት” ኢትዮጵያን በአሓዳዊ ሥርዓት ጠርንፎ ገዛ።

በኢኮኖሚው መስክም፣ የነፃ ገበያ ባልሆነው “የነፃ ገበያ” መንገድ ተጓዘ። “መንግሥታዊ ካፒታሊዝም” ባልሆነው “የመንግሥታዊ ካፒታሊዝም” መንገድ ቀጠለ። ወይንም፣ ብርሃኑ አበጋዝ Political Parties in Business በሚለው እና ሳራ ቮን እና መስፍን ገብረሚካኤል Rethinking Business and Politics in Ethiopia በሚለው ጥናታዊ ፅሑፎቻቸው በትክክል እንዳሉት፤ በየትም አገር እና መንግሥት ታይቶ በማይታወቀው የገዢ ፓርቲ ካፒታሊዝም መንገድ ሄደ። አንድ አማኑኤል ዓለማየሁ የተባለ የሕወሓት ሰው አቦይ ስብሓትን ዋቢ አድርጎ ባቀረበው አንድ ጽሑፍ፦

“አብዮታዊ ዲሞክራሲ በአብዮታዊ ምሁሩ መሪነት የካፒታሊስት ሥርዓትን መገንባት ነው” ብሎ ያለው ሲታወስ፤ የሕወሓት አመራር ለፓርቲ ካፒታሊዝሙ ቲኦሪ ለመፍጠር ሞክሮም እንደነበረ ነው (አይጋ ፎረም፣ ሚያዚያ 16፣ 2010)።

የሕወሓት አመራር በገዢ ፓርቲ ካፒታሊዝም መንገድ የሄደው፣ የ1985ቱ አዋጅ ቁጥር 46 ፦

“ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነትን ያገኘ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎችን መሥራት አይችልም”

በሚል የደነገገ ቢሆንም ኤፈርት የተባለው የሕወሓት አመራር የንግድና ኢንዱስትሪ ድርጅቱ እንደሚታወቀው፤ በኢትዮጵያ አንደኛው ታላቅ ባለንብረት ድርጅት እስከመሆን ደረሶ ነበር።

የሕወሓት አመራር የገዢ ፓርቲ ካፒታሊዝም ግብ፣ የሃብት ምንጮችን መያዝ እና በሃብት ምንጮች ላይ የበላይነቱን ማረጋገጥ እንደነበር ለማሳየት በረጅሙ ማተት አያስፈልግም። የሃብት ምንጮችን የመያዝ ግሥጋሤው ባጭሩ፤ ከ1977ቱ የርሃብ ዘመን አንስቶ ይጀምራል። ከዝያም —ገና በመሣሪያ ትግሉ ዘመን ወልቃይትን እና ራያን የትግራይ አካል በማድረግ ቀጠለ። የሥልጣን ባለቤት ሲሆን ደግሞ፤ የ”ፌደራል” አስተዳደር አካላቱን፣ በኢሕአዴግ አባል ድርጅቶቹ ባለቤትነት ይዞታ ስር አጥሮ አዋቀረ። ወልቃይትን እና ራያን፣ በሕገ—መንግሥቱ ጭምር የትግራይ አካል አድርጎ አፀደቀ።

የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ጥረት፣ ዲንሻ/ቱምሳ እና ወንዶ እያሉ ተከተሉት። የሕወሓት አመራር በ1977ቱ የትግራይ ረሃብ ዘመን በፓርቲው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቱ (para—party NGO) አማካይነት ስላካበተው ሃብት በብዙ ተነግሯል። መንግሥት ሲሆን ደግሞ፤ Government—NonGovernment Organization (GONGO) በሚባለው የመንግሥት—መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቱ ቀጠለበት። የኢሕአዴግ ድርጅቶች በተጨማሪ ደግሞ ፤ ብሔር እና ሃይማኖት የለውም የሚባለው ገንዘብ ሳይቀር፣ በብሔር ስያሜ የተደራጁ ባንኮች ባለንብረት

እስከመሆን ደረሱ። ሌላው ቀርቶ ኳስም፤ በብሔር ድርጅት ቅልጥም የሚጠለዝ ወደመሆን አቀና። ዛሬ ዛሬ ደግሞ፤ የዓለም—አቅፍ ሩጫ አሸናፊ ኢትዮጵያዊያን ሳይቀሩ፤ ለብሔር ሻሞ ቀርቡ። የሕወሓት አመራር የአገዛዙን ዘይቤ እና ሥርዓት በሥራ ላይ ያዋለበትን ስትራቴጂ፤ በጥቂት ነጥቦች ለማጠቃለል ይቻላል።

የሥልጣን ማማ ተቋማትን (ሠራዊት፣ ፀጥታ፣ ፋይናንስ፣ የውጭ ጉዳይ) እና የዲሞክራሲ ተቋማትን (የምርጫ ቦርድ፣ የፍትሕ አካላት፣ መገናኛ ዘዴዎች) የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አገዛዝ መሣሪያ እና ዘብ ማድረግ፣ ኢኮኖሚውን —ብርሃኑ አበጋዝ የገዢ ፓርቲ ካፒታሊዝም ባለው መንገድ ጨቡዶ መያዝ፣ ከአርሶ እና አርብቶ አደሩ እስከ ባለሃብቱ ድረስ ያለውን አምራች እና ነጋዴ ኃይል የገዢው ፓርቲ ካፒታሊዝም አገዛዝ ሥርዓት ጥገኛ ማድረግ፣ የመስተዳደሩን ቢሮክራሲ በድርጅት ካድሬዎች መጠቅጠቅ እና በሙስና መዘፈቅ፣ ውሾቶችን መፈብረክ፣ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን መሰነጣጠቅ እና መፈረካከስ፣ የብሔር እና የሃይማኖት ግጭቶችን መቆስቆስ እና ማራገብ፣ ታሪክን እያጎሳቆሉ በመተረክ አገራዊ/ብሔራዊ ሥነ—ልቦናን እና ማንነትን አኮስሶ መግደል፣ ፀረ—ምሁር ቅስቀሳ ማካሄድ፣ ዕውቀትን ማንጠፍ፣ የምርጫ ውጤቶችን በጉልበት ጭምር በማጭበርበር እና በመጥለፍ ዲሞክራሲያዊ ሂደቶችን እና ክንዋኔዎችን ማኮላሸት እና ቀጣይ የሥልጣን ባለቤትነትን ማረጋገጥ።

ብቻ እንግዲህ—የገዢ ፓርቲ ካፒታሊዝምም እንደሌሎቹ የካፒታሊዝም ዝርያዎች የራሱ ቅራኔዎች እና ቀውሶች አሉት። በሙስና መረብ የተሳሰረ የአገዛዝ ዘይቤም የራሱን ቅራኔዎች እና ቀውሶች ያበቅላል። የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ከጊዜ ጋር እየደረጁ እና የራሳቸውን ማንነት እያጎለበቱ የመጡትን ያህል፤ የሕወሓትን አመራር የበላይነት ወደ መታገል አቀኑ። በውስጥ፣ "ውስጣዊ ዲሞክራሲ" ባሉት ጥያቄ ወጠሩት። ከውጭ፣ በሕዝባዊ ንቅናቄዎች አዋክበው ጥግ አስያዙት። የሕወሓት አመራር በአንድ ወገን መንግሥታዊ ጡንቻውን እየተጠቀመ እና በሌላውም ወገን ተሃድሶ እና ጥልቅ ተሃድሶ እያለ ለመግታት ሞከረ። የማታ ማታ ተሸንፎ እና የበላይነት ሥልጣኑን ተገፎ ወደ መቀሌ አፈገፈገ። በመቀሌ መሸገ። ሄዶ ሄዶ፣ የጦር ኃይል አማራጭን ያዘ።

የፖለቲካ ድርጅት ወደ ጦርነት የሚያመራው፤ ለፖለቲካ ግብ ነው። ዛሬ ብዙዎች "የሕወሓት አመራር የፖለቲካ ግብ ምንድን ነው?" እያሉ ተገቢ ጥያቄ ያነሳሉ። የሕወሓት አመራር በተለያዩ ግዜያት የተለያዩ ግቦችን ስለሚያውጅ፤ የፖለቲካ ግቡን ለይቶ ለማወቅ በውነትም አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ በእኔ እይታ፣ ከቀድሞው ማንነቱ እና አካሄዱ የተለወጠ ነገር የለም። የሕወሓት አመራር ግብ ዛሬም እንደቀድሞው፣ የፖለቲካ ሂደት ክንዋኔን ጠቅልሎ የመያዝ እና ዛሬም እንደቀድሞው የሃብት ምንጮችን በበላይነት የመያዝ ነው።

በስትራቴጂ ረገድ አዲስ ነገር ካለ፤ የሕውሓት አመራር ዛሬ ወደሥልጣን ለማቅናት የሚጥረው፣ የ80ውን የኢሕአዴግ አጋሮቹን "ፌዴራሊስት ኃይሎች" ባላቸው ለመተካት መጣሩ ነው። አሁን አሁን ኦነግ ሸኔ የሚባለውን እና አልሸባብን ለማከል ማቅናቱ ነው። በተረፈ የትንቅንቁን የመጀመሪያ ምዕራፍ መጨረሻ፣ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ይመሰክራል። የሚቀጥለው ምዕራፍ —በእርግጥ ብሳሳት እመርጣለሁ— ከውስጥ እየተጫሩ በሚቀጥሉት እና ከውጭ በማይነጥፉት ጫናዎች ምክንያት፤ እስከ አሁን ከነበረው ባነሰ የተወሳሰበ ይሆናል ብዬ አልገምትም።

## በማኅበራዊ—ፖለቲካ ግብ እና ፕሮግራም የመደራጀት አስፈላጊነት

ከፍ ሲል እንዳመላከትኩት፤ የቀደመው ዘመን ፓርቲዎች የሚፈለፈሉበት ዘመን ነበር። የአሁኑ ደግሞ፣ ክልሎች የሚበረከቱበት ዘመን ሆኗል። ይሁን እንጂ፤ በአንድ ወገን በፌደራሉ ገዢ ፓርቲ እና በመስተዳደሩ መካከል አሁንም ልዩነት የለም። በሌላው ወገን የአስተዳድር ክልሎች የብሔር ድርጅቶች ንብረት ሆነው የተያዙበት እና የሚያዙበት ሁኔታ እንዳለ ነው። በዚህ ከተቀጠለ፤ የፌደራሉም ይሁን የክልል መስተዳድሮች ለጥቀመኝ/ልጥቀምህ መረብ ትስስር እና ለሙስና እንደተጋለጡ መቆየታቸው አይቀርም። በየክልሉ የሚኖሩት የሌሎች ብሔሮች ተወላጆች ተገቢ የዜግነት መብት እንዳልተከበረ ይቀጥላል። ክልሎች በእጅግ የታጠቁ ኃይሎች ባለቤቶች ሆነው እስከቀጠሉም ድረስ፤ ግጭቶችን የሚጋብዙ ሁኔታዎች ሰፍነው ይቀጥላሉ። የዚህን ሁኔታ ፅንፍ ገፅታ ለማስተዋል እሩቅ መሄድ አያስፈልግም። በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተንጣሏል።

ጀርመናይቱ አብዮተኛ ሮዛ ሉክሰምበርግ "የአንዱ ዜጋ መብት የሌላው ዜጋ መብት ከሚጀምርበት ድንበር ላይ ያቆማል" ትል ነበር። የአንዱ ብሔር መብትም፤ የሌላው ብሔር መብት ከሚጀምርበት ድንበር ላይ መቆም ያለበት መብት ነው። ወይንም፤ የብሔር መብት የሌላውን ብሔር እና ዜጋ መብት የመድፈር መብትን አይጨምርም። የኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት ከብሔር ድርጅቶች የመስተዳድር ሥልጣን ባለቤትነት እና ከክልል ድርጅቶች የክልል ባለቤትነት አገዛዝ ሥርዓት እስካልተላቀቀ ድረስ፤ የኢትዮጵያ ፌደራል አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ እንዳልሆነ ይቀጥላል። በማኅበራዊ ፖለቲካ ግብ እና ፕሮግራም ዙሪያ የተሰባሰቡ አገር—አቀፍ ፓርቲዎች በዋናነት የሚናኙበት የአገዛዝ ሥርዓት ዘመን እስካልገለጠም ድረስ፤ ኢትዮጵያ ወደጋራ ወደፊት ምዕራፍ የምትሸጋገርበት ጉዞ በብዙ አኳያ እንደተሰነካከለ ይቆያል።

በአገር—አቀፍ የፖለቲካ ግብ እና ፕሮግራም ዙሪያ ተሰባስቦ መደራጀት እና መንቀሳቀስ የፌደራል አገዛዝ ሥርዓትን አይቃረንም። የብሔሮችን መብት አይፃረርም። ለዚህም እሩቅ መሄድ አያስፈልግም፤ ለብሔሮች መብት ባላት ሰፊ ዕውቅና ከምትሞገሰው ስዊዘርላንድ አንስቶ እስከ ፌዴራል ጀርመን፣ ህንድ፣ ናይጄሪያ እና ሌሎች ድረስ ያሉት የፌዴራል አስተዳደር

አገሮች ፓርቲዎች Social፣ Free፣ Christian፣ Liberal፣ Republican፣ National Democratic፣ Labour እና Green Party በሚባሉ አገር—አቀፍ ፓርቲዎች የሚገዙ ናቸው:: በ60ዎቹ የተመሠረቱት ኢጭአት፣ ኢሕአፓ እና መኢሶን፤ በማኅበራዊ—ፖለቲካ ግብ እና ፕሮግራም ዙሪያ የተሰባሰቡ አገር—አቀፍ ፓርቲዎች ነበሩ:: አገር—አቀፍ ፓርቲዎች መሆናቸው፣ የኢትዮጵያን ብሔሮች መብት ከማወቅ እና ለኢትዮጵያ ብሔሮች መብት ከመታገል አላገዳቸውም::

የምርጫ ቦርድ እንዳስታወቀው፣ ለ2013 የአትዮጵያ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ 20 አገራዊ እና 33 ክልላዊ ፓርቲዎች ተመዝግበው ነበር:: ከ20ዎቹ መካከል የ6ቱ ስያሜ የብሔር ቢሆንም፤ የተመደቡት አገር—አቀፍ ፓርቲዎችን በሚዘረዝረው ክፍል ውስጥ ነው:: በእርግጥም ደግሞ፤ አዋጅ ቁ. 1162 መመርያ ቁ.3፦

“አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አገር—አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ የሚመሠረተው፣ ቢያንስ 10,000 መሥራች አባላት ሲኖሩት እና 15 በመቶ የሚሆኑት ቢያንስ በአራት ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች መሆን አለባቸው::” በማለት ይደነግጋል:: ስለዚህም፤ አንዳንድ የብሔር ፓርቲዎች አገር—አቀፍ ፓርቲ ሆነው መመዝገባቸው አያስገርምም:: የሚያስገርመው ይልቁኑ፤ ሕወሓት—የኢትዮጵያ ብሔሮች ቢያንስ እስከ 15 በመቶ ድረስ በየክልሉ ተሰበጣጥረው እንደሚኖሩ በአዋጅ ጭምር እያወቀ ፤ የፌዴራል አገዛዝ ሥርዓቱን በብሔር ድርጅቶች ባለቤትነት አጥሮ ማዋቀሩ ነው::

ከዚህ ባላነሰ የሚያስገርመው ደግሞ፤ እንደ አገር—አቀፍ ፓርቲ ለመታወቅ ቢያንስ 15 በመቶ የሚሆኑትን ከአራት ክልሎች እንዲያመጡ የተጠየቁት የብሔር ድርጅቶች፣ በብሔር ስያሜያቸው መቀጠላቸው ነው:: ወይንም “አገር—አቀፍ ፓርቲ ነን” ካሉ አይቀር፣ ለማንነታቸው ከላይ እንደተጠቀሱት የፌደራል ሥርዓት አገሮች ያሉ ፓርቲዎች የአገር—አቀፍ ግብ እና ፕሮግራም ፓርቲ ስያሜን አለመምረጣቸው ነው:: ምክንያቱን ማሰብ የሚከብድ አይደለም:: ብቻ እንግዲህ ኢትዮጵያ፣ ሲታገልም “ነፃ አውጭ”፤ ሲገዛም “ነፃ አውጭ” በሆነ “ግንባር” የተገዛች ብቸኛዋ አገር ናት:: እንደ አገር—አቀፍ ፓርቲ የተመዘገቡት የብሔር ድርጅቶች አገራዊ ምርጫዎችን ቢያሸንፉ፤ ኢትዮጵያ በኦፌኮ፣ አብን፣ ኦነግ የምትገዛ ይሆናል:: የመጀመሪያው ትራጄዲ ነበር:: የኋለኛው ኮሜዲ ይሆናል::

ለ2013 አገራዊ ምርጫ እንደአገር—አቀፍ ፓርቲ ከተመዘገቡት 20 ፓርቲዎች መካከል 6ቱ ራሳቸውን የሰየሙት “ዲሞክራቲክ” የምትለዋን ቃል ሰንቅረው ነው:: ከ33ቱ የክልል ፓርቲዎች መካከልም 21ዱ “ዲሞክራቲክ” የምትለዋን ቃል ሰንቅረዋል:: እነዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ

"ዲሞክራቶች" የየክልል አጥራቸውን ተሻግረው ወደአንድ፣ ሁለት እና ሦስት አገር—አቀፍ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ቢሰባሰቡ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ወደፊት እና የጋራ ብልፅግና ይበጅ ነበር። ገዢው ብልፅግና ፓርቲም፤ አጋር ይባሉ የነበሩትን የብሔር ድርጅቶች በአባልነት ከመቀበሉ እና አንዳንድ አባላቱን ከመሸኘቱ ውጭ፤ አሁንም የሚታወቀው በኢሕአዴጋዊ አደረጃጀት ተዋቅሮ ነው። ብልፅግና በአንድ የጋራ አመለካከት፣ ዓላማ እና በአንድ የፖለቲካ—ማኅበራዊ ፕሮግራም ሥር የተሰባሰቡ ግለሰቦች ፓርቲ ወደ መሆን እስካላመራ ድረስ፤ ወደ ማዕዘን አንድ የመመለሱ ዕድል ከፍተኛ ሆኖ ይታየኛል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ግን፤ በፖለቲካ ቃላት እና ፅንሰ—ሃሳቦች አረዳድ እና አጠቃቀም ረገድ ያሉትን ችግሮች ማጥራትም ጠቃሚ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። አንዳንዶቹን እንደሚከተለው ለማስታወስ ይቻላል።

## ስለ ቃላት እና ፅንሰ—ሃሳቦች አረዳድ እና አጠቃቅም

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ዓለም ውስጥ ግንባር ያልሆኑ ድርጅቶች ራሳቸውን "ግንባር" እያሉ ይጠራሉ። ፓርቲም ያልሆኑ ድርጀቶች ራሳቸውን "ፓርቲ" እያሉ ይጠራሉ። እንደሚታወቀው፣ "ግንባር" የራሳቸው የተለየ ማንነት ያላቸው ነፃ ድርጅቶች በተወሰነ ግብ እና በጊዜ ለተገደበ የጋራ ጉዳይ በጋራ የሚመሠርቱት የድርጅቶች ድርጅት ነው። በኢትዮጵያ ራሳቸውን "ግንባር" ብለው ከሚጠሩት ድርጅቶች መካከል ትሕነግ እና ኦነግ የሚባሉትን ብንወስድ እንኳን፤ ግንባሮቹ ስንት ነፃ ድርጅቶችን በአባልነት እንዳቀፉ አይታወቅም። ምናልባት፣ ኢሕአዴግ "አራት ድርጀቶችን ያቀፍኩ ነኝ" ይል ስለነበር፤ ግንባር ሊባል ይችል ይሆናል። የሕወሓት አመራር ከኢሕአዴግ አመሠራረት ጀምሮ የሄደበት መንገድ ስለሚታወቅ፤ መዘርዘር አያስፈልገውም።

"ፓርቲ" የሚለው ቃልም ቢሆን ፤ የጋራ አመለካከት፣ ዓላማ እና አንድ የፖለቲካ—ማኅበራዊ ፕሮግራም ዕቅድ ያላቸው ግለሰቦች በአንድ የተሰባሰቡበት አሓድ ነው። በቅራኔዎች አረዳድ እና አቀማመጥ ረገድ የጋራ ትንተና እና አመለካከት ያላቸው ግለሰቦች በአንድነት የተሰባሰቡበት ድርጅት ነው። እንዲያም ሲል፣ እንደ አንድ አሓዳዊ የፖለቲካ ተፅእኖን ለማሳረፍ፣ በምርጫ ለመወዳደር እና የመስተዳድር ሥልጣንን ለመቆጣጠር የተደራጀ ነው። በተግባሩም፣ የፖሊሲ መመሪያዎችን እያረቀቀ እና መግለጫዎችን እያወጣ ለመራጩ ሕዝብ ያሳውቃል። ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎችን በየዕለቱ እና በየወቅቱ ይገመግማል። መራጩን ሕዝብ በግምገማው መሠረት ያስተምራል፤ ያነቃል፤ ያደራጃል። እንደዚሁም፣ ለሉዓላዊነት መከበር እና ለግዛት አንድነት ይቆማል። ለአገራዊ ፖለቲካ መረጋጋት እና ስክነት ይሠራል። አባላቱን እያሰለጠነ ለመሪነት ያበቃል። አመራሮችን ያወጣል። በምክር ቤት ሕይወት ውስጥ ሲሳተፍ፤ የምክር

ቤቱን ሥራ ማቀላጠፍ ያስችላል። የምርጫ ቦርድ ከመዘገባቸው 53 ፓርቲዎች መካከል ስንቶቹ የተመለከቱትን የፓርቲ መገለጫ እና መስፈርቶቸን እንደሚያሟሉ እርግጠኛ አይደለሁም።

በአሓዳዊ እና በፌዴራላዊ የአገዛዝ ሥርዓቶች አረዳድ እና አጠቃቀም ረገድም እንደዚሁ ችግሮች አሉ። አሓዳዊ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ የአግዛዝ ሥርዓቶች በዚህች ዓለም በርካታ ናቸው። ይሁንና፣ አንዳንድ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ተዋናዮች የአሓዳዊ አገዛዝ ሥርዓትን ምንነት ለመግለፅ እና ለማስተዋወቅ የሚጥሩት፤ በኢትዮጵያ የንጉሠ—ንግሥታዊ እና የወታደራዊ አሓዳዊ አገዛዝ ሥርዓት ዓይነት ብቻ ወስነው ነው። የፌደራል ሥርዓትንም በሚመለከት፤ ፌደራላዊ ላልሆነው ለኢትዮጵያ "ፌዴራላዊ" ሥርዓት ሲሞግቱ ይደመጣሉ። እንደዚህ ዓይነት ፓርቲዎች መራጩን ሕዝብ ምኑን የሚያስተምሩ፣ ምኑን የሚያነቁ እና ለምን እንደሚያደራጁ ለመረዳት የሚቻል አይደለም። ይሁንና፣ ድርጅቶቹ እና ተዋናዮቹ የፖለቲካ ቃላቶችን እና ፅንሰ—ሃሳቦችን አነሰ ሲባል ለጥጠው፣ ያለዚያም አዛብተው የሚረጩት ያለ ምክንያት እንዳልሆነ ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም።

ዕውቁ የፖለቲካ ሳይንቲስት ጂዮቫኒ ሳርቶሪ እንዳሉት፡—

"ፅንሰ—ሃሳቦች እየተለጠጡ የሚዛቡት፣ የማኅበራዊ—ፖለቲካ ጉዳዮች አረዳድን ሆን ብሎ እሴት-አልባ አድርጎ ለመጠቀም ነው"።

የሳርቶሪን ሌላ ጽሑፍ ጠቅሰው ማይምሬ መናሰማይ እንዳሉት ደግሞ፡—

> "አንድ ፅንሰ—ሃሳብ የሚለጠጠው እና የሚዛባው፤ ፅንሰ—ሃሳቡ የሚሸፍነው መሠረታዊ ትርጉም ወዲያ ተጥሎ እና ተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮችን እንዲሸፍን ለማድረግ ሆን ተብሎ ሲለጠጥ እና በሥራ ላይ ሲውል ነው። በውጤቱ ለጊዜው የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝ ቢመስልም፤ የመጨረሻ መጨረሻ ስለነገሮች ሊኖር የሚገባውን በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ አረዳድ እና ግንዛቤ የሚያኮስስ ይሆናል።"

አስከትሎም ለማለት ይቻላል፤ የድርጅት አባሎችን እና ተከታዮችን ወደ "መንጋ" አውርዶ የሚቀሰቅስ እና የሚያሰልፍ አካሄድ ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ "መንግሥት" የሚለው ቃል ለመንግሥት (state) እና ለመስተዳድር (government) ይውላል። ለአንድ ፍፁማዊ ግለሰብ ወይንም ፓርቲ አገዛዝ መስፈን አመቺ ሁኔታን ያሰፈነው አንድ መሠረታዊ ጉዳይም፤ ይህ ይመስለኛል። ሲጀመር፤ ገዢዎቹ ራሳቸው ሆኑ ወይንም ሕዝብ፣ በመንግሥት ሥልጣን እና በመስተዳደር ሥልጣን መካከል ተገቢውን ልዩነት እንዳያደርጉ ያደርጋል። ስለዚህም ይመስለኛል፤ በኢትዮጵያ ምድር የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠ የሰዎች ቡድን ሁሉ መንግሥትን እና መስተዳደርን የግል ንብረቱ አድርጎ እስከመያዝ የሚዘልቀው፣ ሶስቱ የመንግሥት አካላት የሚባሉት ተለያይተው የታወቁት፣መንግሥታዊ ተቋማት እና ድርጅቶች ውስጣዊ ራስ ገዝነት ኖሯቸው የማያውቀው፣ የፖለቲካ እና ማኅበራዊ

ጥያቄዎችምለመስተዳደሩ ሳይሆን ለመንግሥት እየቀረቡ የሚደመጡት፣ ወቀሳ እና ሙገሳም ለመስተዳደር ሳይሆን ለመንግሥት የሚቸሩት።

በነዚህ የመጀመሪያ ጉዳዮች ረገድ አንድ ዓይነት አረዳድን እና አንድ ዓይነት አጠቃቀምን ለማስቻል ጥረት ቢደረግ አንዳንድ የፖለቲካ—ማኀበራዊ ውዥንብሮችን ለመቀነስ የሚጠቅም ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ገዢ ፓርት እና መስተዳደር ሥፍራ ሥፍራቸውን እንዲይዙ እና ሚና ሚናቸውን በአግባቡ እንዲጫወቱ ለማድረግ ይረዳል ብዬ አስባለሁ። አሁን አሁን "አገረ—መንግሥት" የሚለውን ቃል መጠቀም ተጀምሯል። ይህም እንደ ላይኞቹ፣ ሁልጊዜም እና በየትም ሥፍራ በአንድ ዓይነት አረዳድ እና በአንድ ዓይነት አጠቃቀም በሥራ ላይ የዋለ አይመስለኝም።

አትዮጵያ ሌላም፤ የሲቪል አገልግሎት ኮሚሽን እና የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ባለቤት ናት። ይሁን እንጂ፤ የመስተዳደር ተቋማት ተቀጣሪዎች የሚታወቁት "የመንግሥት ሠራተኞች" በሚል ነው። የፌደራሉ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁ. 1064/2017፣ ተቀጣሪዎቹን በአዋጅ ጭምር የሚጠራቸውም፦

> "የመንግሥት ሠራተኛ ማለት፣ በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው"

እያለ ነው። "የመንግሥት ሠራተኛ" ከማለት ይልቅ፣ አንግሎ-ሳክሰንስ እንደሚጠሯቸው civil servant (ሌላ ቃል ስላጣሁ—የማኀበረሰብ አገልጋይ) ቢባሉ እና የሚሰጡትም አገልግሎት "የማኀበረሰብ አገልግሎት" በሚል ቢታወቅ፤ ማንነታቸውን እና ምንነታቸውን በተሻለ የሚያመለክት ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ።

አንግሎ-ሳክሰንስ እንደዚሁም፤ በcivil servant እና በpublic servant መካከል ግልፅ ልዩነት ያደርጋሉ። የተጠቀሰው አዋጅ "public service" የሚለውን ቃል ጭምር ተጠቅሞ ሲያበቃ የሚነበበው ግን፦

> "'ሚኒስቴር' ወይንም 'ሚኒስትር' ማለት እንደ ቅደም-ተከተሉ የፐብሊክ ስርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ወይንም ሚኒስትር ማለት ነው" እያለ ነው።

የሚያስገርመው፣ በትምህርታቸው፣ በሙያ ክህሎታቸው እና በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በpublic service ውስጥ ሊካተቱ ይገባቸው የነበሩት ዳኞች፣ ሐኪሞች፣ መምህራን፣ የእሳት አደጋ እና የማህበራዊ ሠራተኞች እና የመሳሰሉት በአዋጁ ውስጥ አልተዘረዘሩም።

እነዚህን የመሳሰሉት ቃላት እና ፅንሰ—ሃሳቦች በአግባቡ በጥቅም ላይ ቢውሉ፤ የኢትዮጵያን መስተዳደር አገልግሎት ከአብዮታዊ ሰደድ እና ከኢሠፓ ዘመን ጀምሮ እስከ ኢሕአዴግ እና ብልፅግና ፓርቲ ድረስ የተጠናወተው የ "መንግሥት ተቀጣሪ" ካድሬ ሠራዊት ዘመን የሚያበቃበት ምዕራፍ ሊከፈት ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ማለትም፣ "ምን ትፈልጋለህ?" እያለ

ከሚያመናጭቅ ካድሬ፤ "ምን ልታዘዝ?" ውይንም "ምን ልርዳ" እያለ የሚጠይቅ ሥልጡን ቢሮክራት ዘመን ሊከፍት ይችላል። ከዚህም ባሻገር የሚመሰገነውን እና የሚወቀሰውን ግለሰብ/ቢሮክራት በቅጡ ለመለየት የሚረዳ ይሆናል። የኢትዮጵያ የቋንቋ ሊቃውንት በዚህ ረገድ ቢረዱ ጠቃሚ ይሆናል።

## ማጠቃለያ

የ1983 ሽግግር—በወደፊት ተመልካችነት መንፈስ፣ አካታች እና አሳታፊ ሆኖ ቢመራ እና ቢካሄድ ኖሮ፤ የአዲሲት ኢትዮጵያ መሥራች ሽግግር በሆነ ነበር። የፌዴራል አገዛዙ ሥርዓት በብሔር ድርጅቶች ባለቤትነት ታጥሮ የተዋቀረ ባይሆን ኖሮ፤ የዜጎች መብቶች በተሻለ ይከበሩ እና ይጠበቁ ነበር። ለካፒታል፣ ለምርት መገልገያዎች እና ለምርት ኃይሎች ነፃ አገራዊ እንቅስቃሴ እና ዕድገት የተሻለ አመቺ ሁኔታ ይፈጠር ነበር። የ1997 ምርጫ እንደ አጀማመሩ ውጤቱም ቢከበር ኖሮ፤ መሥራች ምርጫ በሆነ ነበር። የ2010ን የኢሕአዴግ ውስጥ ትንቅንቅን ይፋውጤት ሕወሓት በፀጋ ቢቀበል እና የለውጡ አካል ሆኖ ቢቀጥል ኖሮ፤ የጥቅምት 2013ቱ ክስተትከታሪካችን ገፆች ውስጥ ባልገባ ነበር። በዚህ ሰዓት የሚካሄደው አስከፊ ጦርነት አብቅቶ የሰላማዊ ድርድር ዘመን የሚከፈትበት ምዕራፍ ሩቅ እንዳይሆን እመኛለሁ።

2015 በኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር የሚጀመርበት ዓመት እንደሚሆን ይጠበቃል። ምክክሮቹ በጋራ ወደፊት ተመልካችነት መንፈስ እና በተገቢው አካታች እና አሳታፊ መንገድ ተከናውነው፤ የአዲሲት፣ ሰላማዊት እና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መሥራች ምክክሮች እንዲሆኑ እመኛለሁ። ማለትም፣ የ"ቢሆን ኖሮ" ዘመን የሚያበቃበት። ከጠብመንጃ ይልቅ፣ በወደፊት ተመልካች አተያይ የዲሞክራሲያዊ ሃሳብ እና አማራጭ ልዕልና የሚገዛበት፣ ገዢ ፓርቲ እና መስተዳደር የተለያዩበት፣ የሥራ አስፈፃሚ፣ የምክር ቤት እና የፍትሕ አካላት ተገቢ ሥፍራቸውን የሚይዙበትን እና ተገቢ ሚናቸውን በነፃነት የሚጫወቱበት እና የመስተዳደር ተቋማት ውስጣዊ ነፃነትን የተጎናፀፉበት እንዲሆን እመኛለሁ።

በመጨረሻ ግን፤ ዲሞክራሲ ስል ራሳቸውን ኢንተርናሺናል ኮሚኒቲ እያሉ የሚጠሩት የምዕራቡ ኃያላን መንግስታት የተፈጥሮ ሕግ ያህል አድርገው በገንዘብ፣ በመገናኛ ዘዴዎች፣ በዕቀባ፣ በመሣሪያ እና በአቤት ባዮቻቸው ሊጭኑብን የሚፈልጉትን ኒዮ—ሊበራል ዲሞክራሲ ማለቴ እንዳልሆነ መግለፅ እፈልጋለሁ። በአንፃሩ፣ በኢትዮጵያዊያን፣ለኢትዮጵያዊያን የሚሆነውን እና የሚበጀውን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ማለቴ ነው።

በዚህ መንፈስ፣ የዛሬው ቀዳማዊ የሪፎርም ጥያቄ፣ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነውን "የፌዴራል" አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ የማድረግ ሪፎርም ነው ብዬ አምናለሁ። ይህም የሕገ—መንግሥቱን መሻሻል አጥብቆ ይጠይቃል፣ በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት መካከል የሚኖረውን ቀጥታ

**እና የአግድሞሽ ግንኙነት በዝርዝር መወሰንን ይጠይቃል፣ ክልሎችን ከቋንቋ መሥፈርት ባሻገር ሄዶ ማዋቀርን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ መክሮ እና ዘክሮ ለጋራ ወደፊት በጋራ ለመጓዝ ከተነሳሳ፤ ይቻላል። "ይቻላል" ትርጉም የሚኖረው ግን፣ ወደ ተግባር እና ነባራዊ ጭብጥ ተለውጦ ሲታይ እና ሲዳሰስ ነው።**

# ዋቢ መፅሀፍት

ዓለማየሁ ገዳ፣ የነጋደራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ መሠረታዊ የኢኮኖሚክስ አስተሳሰቦች (2013)

Bahru Zawde, Pioneers Of Change in Ethiopia (2002)

Bahru Zawde, Legacies of the Ethiopian Student Movement (2015)

Berhanu Abegaz, Political Parties in Business (2011)

Bruce Berman, Ethnicity, Patronage and the African State (1998)

Christopher Clapham, State, Society and Political Institutions in Revolutionary Ethiopia

Elleni Centime Zeleke, When Social Science Concepts Become Neutral (2016)

Gebru Tareke, Ethiopian Revolution (2009)

Giovanni Sartori, Concept Misformation in Comparative Politics (1970)

IDEA, Funding of Political Parties and Election Campaigns (2014)

Jean-Nicolas Bach, Abyotawi democracy: Neither Revolutionary nor Democratic (2011)

Jon Abbink, Discomfort of Democracy in Ethiopia (2006)

Liam D. Anderson, Federal Solutions to Ethnic Problems: Accommodating Diversity (2012)

Lovise Aalen & Kjetil Tronvoll, Curtailing Political and Civil Rights in Ethiopia (2009)

Maimire Mennasemay, Horn of Africa as a Democratic Project: Some Conceptual Issues (2007)

R.R. Balsvik, Haile Selassie's Students, MI: African Studies Center, Michigan (1985)

S. Vaughan & M. Gebremichael, Rethinking Business and Politics in Ethiopia (2011)

William Engdahl, Manifest Destiny: Democracy as Cognitive Dissonance (2018)

Wondwosen Teshome, Ethiopian Opposition Political Parties and Rebel Front (2009)

Wondwosen Teshome, Political Finance in Africa: Ethiopia as a Case Study (2009)

የራስወርቅ አድማሴ፣ ሥርዓታት፣ የፖለቲካ ነፃነት እና ልማት በኢትዮጵያ

## ስለጥናታዊ ፅሁፎ አቅራቢዎቹ አጭር ገለፃ



**ዶ/ር አስናቀ ከፋለ** ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም ጃፓን አገር ከሚገኘው ኢንተርናሽናል ዩኒቨርስቲ ኦፍ ጃፓን በዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምሕርት ዘርፍ የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በመቀጠልም ከላይደን ዩኒቨርስቲ (ኔዘርላንድስ) የዶክተሬት ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል። ዶ/ር አስናቀ በአስተዳደር፣ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ግጭትና የግጭት አፈታትን ጨምሮ በተለያዩ በተለያዩ ፖለቲካዊና አለማቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ጥናታዊ ፅሁፎችን ያቀረቡ ሲሆን በተለያዩ የአካዳሚ ጆርናሎች እና መፃሕፍት ላይ አሳትመዋል። በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የጥናትና ህትመት ዳይሬክተር በመሆንም አገልግለዋል። በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምሕርት ክፍል በተባባሪ ፐሮፌሠርነት እና በከፍተኛ ተመራማሪነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።



**ዶ/ር ኃይለየሱስ ታዬ** በ1988 ዓ.ም. ጀርመን አገር ከሚገኘው የማረቲን ሉተር ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካ ሳይንስ የማስተርስ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፌደራል ስተዲስ ማዕከል በ2008 ዓ.ም. ተቀብለዋል።

በተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃ ያገለገሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል በአማራ ክልላዊ መስተዳድር በሰራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚ/ር የአቅም ግምባታ ሀላፊ፣ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ በመምህርነትና በዲንነት እንዲሁም በአፍሪካ ሊደርሺፕ ኤክሰለንስ አካዳሚ የአካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክተር በመሆን ከጥር 2009 ዓ.ም - መስከረም 2013 ዓ.ም.ድረስ አገልግለዋል

ዶ/ር ኃይለየሱስ ታዬ በአሁኑ ሰአት የፌደራል ጥናት ረዳት ፕ/ር ሲሆኑ በፌደሬሽን ምክር ቤት የሕገ-መግስትና እና የፌደራሊዝም ስልጠና ማዕከል ዳይሬክተር ጀነራል ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡



**ፕሮፌሰር ገብሬ ይንቲሶ** የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሶሲዮሎጂ እንዲሁም የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሶሻል አንትሮፖሎጂ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተከታተሉ ሲሆን፤ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ደግሞ አሜሪካን አገር ከሚገኘው የፍሎሪዳ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል አንትሮፖሎጂ አግኝተዋል። ፕሮፌሰር ገብሬ በሕዝብ እንቅስቃሴ፣ ስደትና ስደተኛ ጉዳዮች፣ ግጭትና የግጭት አፈታት፣ መልሶ ማቋቋምና በሲቪክ ማኅበራት ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ በርካታ ጥናታዊ ፅሑፎችን አሳትመዋል። ፕሮፌሰር ገብሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶስዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ የትምህርት ክፍል ለበርካታ ዓመታት በከፍተኛ መምህርነት ያገለገሉ ሲሆን የትምህርት ክፍሉ ሊቀመንበር እንዲሁም ለተወሰኑ አመታት የሶሻል ሳይንስ የትምህርት ክፍል ዲን ሆነው ሰርተዋል። በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ክልል በሚገኘው የጂንካ ዩኒቨርሲቲን በማቋቋም እና የዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያው ፐሬዚዳንት በመሆን አገልግለዋል።



**አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ** በቀድሞ አምቦ እርሻ ት/ቤት፣ ሃረማያ ኮሌጅ የግብርና ትምህርትን የተከታተሉ ሲሆን፤ በጀርመን አገር ቆይታቸው ደግሞ የፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት ወስደዋል ፤ የመኢሶን መሥራች እና የመፅሔት ቦርድ አባልም ነበሩ፤ በመስከረም 1967 ወደ አገራቸው ተመልሰው በመሬት ይዞታ አስተዳደር እና በየካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤት አገልገለዋል ፤ በ1971 በነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት በስደት ከአገር የወጡ ሲሆን፤ **"በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ"** የተሰኘውን መፅሐፋቸውን በ1991 ዓ.ም. አሳትመዋል፤ በስደት ቆይታቸው የተለየዩ ፅሑፎችን ለአገር ውስጥ ጋዜጦች ላይ በማቅረብ ይታወቃሉ፤ በቅርቡም፣ የነዚህን ፅሑፎች ስብስብ "**ቅን ፍላጎት ካለ መንገድ አለ"** በሚል ርዕስ አሳትመዋል። ለ20 ዓመታት ያህል በምዕራብ እና ምሥራቅ አፍሪካ አገራት ውስጥ በሚገኙ የሰብዓዊ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጣሪ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን በአሁን ሰአት በደቡብ ሱዳን የአፍሪካ ሂዩማኒቴሪያን አክሽን ሰብአዊ ድርጅት ተወካይ ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።